Biglife® /

# ደቀ መዛሙርትን የሚያፈሩ፥ ደቀ መዛሙርት ማፍራት

**ሞጁል 1 - አጭር መመሪያ**

ፍቅር. መታዘዝ. መብዛት.

# አጭር የስልጠናው መግለጫ

“ለእኛ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ ለእኛ ሳይሆን፣ ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ፣ ለስምህ ክብርን ስጥ።”

- መዝሙር 115፥1

ክርስቶስ የሚከተሉትን ሁሉ ሲጠራቸው እግዚአብሔርን እንዲወዱ፣ ሌሎችንም ሰዎች እንዲወዱ እና ብዙ ደቀ መዛሙርትን የሚያፈሩ ደቀ መዛሙርት በምድር ዙሪያ መፍጠር ነው።

ቢግላይፍ የደቀ መዝሙር ስልጠና ብዙ ክርስቲያኖች ወንጌልን የማያካፍሉበትን እና ደቀ መዝሙር ማድረግ የማይችሉበትን ምክኒያቶች አስወግደው ወደ እዚህ ሙሉ የሆነ ደስታ ህይወት ውስጥ እንዲገቡ የሚረዳ ነው። ከእነዚህ ምክኒያቶች ውስጥ ሁለቱ፡ “ለዚህ አገልግሎት አልተጠራሁም” እና “የሚገባው ስልጠና የለኝም” የሚሉት ናቸው። ነገር ግን በአገልግሎት ላይም ሆነ በገበያ ቦታ፡ እኛ የተጠራነው እግዚአብሔርን እንድንወድ፣ ሌሎችንም ሰዎች እንድንወድ እና ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ ነው። ይህ ስልጠናም የሚሰጣችሁን የመርጃ መሳሪያዎች ወደ ተግባር እንድትለውጡት ያበረታታችኋል።

ቢግላይፍ ስልጠና በማቴዎስ ወንጌላ 28፡ 19-20 በተጠቀሰው መሰረት **ለምን** ሁላችንም ወንጌልን ለማብሰር እንደተጠራን እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን “4ቱ ጥሪዎች” ያስተምረናል።

ከዚያም ቢግላይፍ አማኞች **ለማን** ወንጌልን ማብሰር እንዳለባቸው እና **እንዴት** ደግሞ የራሳቸውን የህይወት ታሪክ (ምስክርነት) እና የእግዚአብሔርን ታሪክ (ወንጌልን) በባህል በማይነቀፍ መልኩ ማቅረaብ እነደሚችሉ በማሳየት ይረዳቸዋል።

በተጨማሪም አማኞች ሰዎችን “የህይወት ደቀ መዝሙር” በሚባል ቡድን ውስጥ አስገብተው እንዴት እነዚህን ሰዎች በህይወታቸው ደቀ መዛሙርት እንደሚያደርጉ ያስተምራቸዋል። ቡድን ብለን የምንጠራቸው ከ 10 አመት ህፃን አንስቶ እስከ 80 አመት አዋቂ ድረስ ያጠቃልላል። ደቀ መዝሙር በማድረግ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔርን መስማት፣ ማዳመጥ፣ መታዘዝ እና ለሌሎች የሰማነውን ማስተላለፍ ዋና ነገር ነው። ስለዚህ አንድ ቡድን ደቀ መዝሙር ለማድረግ 3 ክፍል ያለውን ሂደት ይከተላል። የመጀመሪያው ክፍል ተጠያቂነትን በተመለከተ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተሳትፎ የሞላበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሲሆን ሦስተኛው ክፍል በህይወት መተግበርን (መስማትን እና መታዘዝን)ያካተተ ነው። እዚህ ቡድን ውስጥ ህብረት የማድረግ ጊዜ፣ የፀሎት እና የዝማሬ ጊዜም ተካትቷል። ይህን ቡድን መምራት ቀላል ስለሆነ፡ ሌሎች ተመሳሳይ ቡድኖችን መፍጠር ቀላላ ነው። ስለዚህ አዲስ አማኞች እንዴት የራሳቸውን የህይወት ታሪክ እና የእግዚአብሔርን ታሪክ ባላቸው እድል ሁሉ መናገር እንዲችሉ እንደሚሰለጥኑት ሁሉ ፤ እንዴት በማባደን ሂደት ውስጥ አዲስ አማኞችን ደቀ መዝሙር ማድረግ እንደሚችሉም ይሰለጥናሉ። አዳዲስ ቡድኖች በሚፈጠሩበት ጊዜ፡ ከሌሎች ቡድኖች ጋር በቅርበት እንዲሰሩ፣ የማይቋረጥ የመሪነት ትምህርት እና ስልጠና እንዲሰጠቸው ይደረጋል። አንዳንድ ጊዜም እነዚህ ቡድኖች ለየት ያለ የወንጌል ስርጭት ላይ ለመሳተፍ ወይንም ክልላዊ በዓል ለማክበር በአንድ ላይ ይሰበሰባሉ።

እንደ የፀሎት ጉዞ፣ የፀሎት ሳይክል እና የተጠያቂነት ቡድን የመሳሰሉ የደቀ መዝሙር ማድረጊያ መርጃ መሣሪያዎች በዚህ ስልጠና ውስጥ ይካተታሉ። ደቀ መዛሙርትን የማፍራት እና የማብዛት መርህዎች፡ ለምሳሌ የሰላም ሰዎችን መፈለግ፣ የ**ም.እ.ማ.መ.** ዘዴን (ምሳሌ፣ እርዳታ፣ ማየት፣ መልቀቅ)በመጠቀም አዲስ ቡድን መፍጠር እና ሁሉንም አማኞች “እራስን የመመገብ” መርህዎችን ማስታጠቅ በዚህ ስልጠና ውስጥ ከሚካተቱ ትምህርቶች ናቸው።

በስልጠናው መጨረሻ፡ ሰልጣኞች የ3 ወር ቃል መግቢያ ቅፅ ይሞሉና የቢግላይፍ አሰልጣኞቸው የሰጣቸውን የደቀ መዝሙር መርጃ መሣሪያ እንዲጠቀሙ በመምከር እና ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ በመርዳት ለሚቀጥሉት ወራት እነርሱን ይከታተላል። የተማራችሁትን የመርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም እና በየሳምንቱ በየቡድናችሁ እግዚአብሔር የሚናገራችሁን በብዙ ፀሎት እና መታዘዝ ውስጥ፡ ብዙ ደቀ መዛሙርትን የሚያፈሩ ደቀ መዛሙርት የማፍራት እንቅስቃሴ ልትጀምሩ ትችላላቹህ።

ይህ የደቀ መዛሙርትነት እንቅስቃሴ ብለን የምንጠራው ኢየሱስን በታማኝነት በሚታዘዙ ደቀ መዛሙርት አማካኝነት ከተማችሁን፣ ክልላችሁን፣ ሀገራችሁን እንዲሁም አለምን ሊያጥለቀልቅ ይችላል።

## ፍጥነት

- ፍጥነት ዋና ነገር ነው። የቤተ ክርስቲያን የእድገት ፍጥነት ከአለም ህዝብ ብዛት እድገት ጋር እየተመጣጠነ አይደለም። የእግዚአብሔር መሻት ምድርን በክብሩ መሙላት እስከሆነ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን የእድገት ፍጥነት ከምድር ህዝብ እድገት የፈጠነ እንዲሆን ደቀ መዛሙርትን የሚያፈሩ ደቀ መዛሙርት ማፍራት አለብን።
- በግምት በእያንዳንዱ ሴኮንዶቹ አንድ ሰው እየሞተ ወደ ገሃነመ እሳት እየተጓዘ ነው።

## የቢግላይፍ ተልዕኮ

- የቢግላይፍ ተልዕኮ፣ "በዓለም ዙሪያ ያሉ አማኞችን የራሳቸውን ህብረተሰብ በወንጌል እንዲደርሱና ለኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር እንዲያደርጉ ማስታጠቅ ነው።"

## የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት . . . እና ማድመጥ

ልምምድ: **የተለመደው መግቢያ።**

ልምምድ: **የመስማት መግቢያ።**

**ስለ የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት እና ማድመጥ የሚናገሩትን የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች ተመልከቱ**

- የዮሐንስ ወንጌል 5፥19
- የዮሐንስ ወንጌል 8፥47
- የዮሐንስ ወንጌል 10፥27
- የዮሐንስ ወንጌል 16፥13-14

# የደቀ መዝሙር ትርጉም

**ከዌብስተር ኒው ወርልድ መዝገበ ቃላት የተገኘ የደቀ መዝሙር ትርጉም**

1. የአንድ አስተማሪ ወይም ትምህርት ቤት ተማሪ ወይም ተከታይ
2. የቀደሙት የኢየሱስ ተከታዮች
3. አንድን ዶግማ ተቀብሎ ወደሌሎች በማስፋፋት የሚሳተፍ

*“ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”*

- የማቴዎስ ወንጌል 28፥19-20

**የደቀ መዝሙር ትርጉምን በሦስት ክፍል አስቡት ፡**

“**የሚቀበል፣ የሚታዘዝ ፡** እና የኢየሱስን ትዕዛዛት **የሚያስፋፋ**”

# የዕድገት መለኪያ




**እውቀት መታዘዝን እና ማስፋፋትን ወደ ኋላ ማስቀረት የለበትም!**



*“ታዛዥ ከመሆን በፊት ለመረዳት ከመሞከር ይልቅ፣ በመታዘዝ ውስጥ እንረዳለን።”*

- በፓኪስታን የሚገኙ የቢግላይፍ መሪዎች

# የቤተ ክርስቲያን ትርጉም

**ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በ ሦስት መንገድ ተገልፆ ይገኛል።**

1. አለም አቀፉ ቤተ ክርስቲያን [ማቴ. 16፥18]
2. የከተማ ወይም የክልል ቤተ ክርስቲያን [ራእ. 3፥1]
3. በቤት ለቤት ስብሰባ ያለቸ ቤተ ክርስቲያን [ሐ.ሥ. 5፥42፤ Col 4፥15]

ኢየሱስ በ ማቴ.22፥36-40 እንደተናገረው በብሉይ ኪዳን የሚገኙት የእግዚአብሔር ትዕዛዛትን ጠቅለል አድርጎ የሚይዘው እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ማንነትህ ውደድ የሚለው እና ጎረቤትህንም እንደ ራስህ ውደድ የሚሉት ናቸው። **ደቀ መዛሙርት ማድረግ** በሚለው ደግሞ በአዲስ ኪዳን የሚገኙትን የጌታን ትዕዛዛት ጠቅልሎ ይይዛል። ምክኒያቱም ደቀ መዛሙር ማድረግ የሚለው ቃል የጌታን ትዕዛዛት እንዲጠብቁ ማስተማርንም ያጠቃልላል።

ቤተ ክርስቲያናት የምንላቸው እግዚአብሔርን የሚወዱ፣ ሌሎችን የሚወዱ እና ደቀ መዛሙርት የሚያደርጉ መንፈሳዊ ቤተ ሰብዎች ናቸው። እነዚህን ቤተ ክርስቲያናት እንደ እግዚአብሔርን የሚወዱ፣ ሌሎችንም የሚወድዱ እና ደቀ መዛሙርትን የሚያበዙ መንፈሳዊ ቤተሰብ አድርገን ትርጓሜ እንሰጣቸዋለን። ይህ ትርጉም ግን የቤተ ክርስቲያን ህንፃን፣ የሚቀጠሩ ሰዎችን፣ ገንዘብን ወይም ፕሮግራሞችን አያካትትም። ይህንም ያላካተተው አላስፈላጊ ሆነው ሳይሆን የማብዛት ስራው ላይ ነገሮችን አዳጋች ስለሚያደርግ ነው። ቀለል ያሉ ነገሮችን በቀላሉ ለማብዛት ስለሚቻል እነዚህን ያልተካተቱትን ነገሮች ቤተ ክርስቲያኑ ወደ ከተማ ወይም ወደ ክልላዊው ቤተ ክርስቲያን በሚያድግበት ጊዜ እንዲካተቱ ተተናቸዋል።




“ቤተ ክርስቲያን” የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ኢክሌዢያ ማለት ነው። ይህ የግሪክ ቃል ትርጓሜም “በአንድነት እንዲሰበሰቡ የተጠሩ” ማለት ነው። ህንፃን፣ የቅስና አገልግሎትን፣ የሰንበተ እሁድ ጠዋት ፕሮግራሞችን ሳይሆን ክርስቶስ በአንድነት እንዲሰበሰቡ ከዚህ አለም የጠራቸውን ሰዎች ያመለክታል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን በአንድነት በአንድ ስፍራ በተሰበሰቡ ሰዎች ሊከናወኑ ይቸላሉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተ ክርስቲያን ትርጉም አይደሉም። በሚቀጥሉት የስልጠና ጊዜአቶች ሁሉ ደቀ መዝሙር ለማድረግ የሚሰበሰቡትን እና እግዚአብሔርን እና ሌሎችንም ለመውደድ እየፈለጉ ህብረት የሚያደርጉትን አማኞች “ህብረት” ብለን እንጠራቸዋለን።

# ማብዛት

**ቀለል ያሉ ነገሮች በቀላሉ ይባዛሉ**

- የምትጠቀሟቸው ነገሮች ወይም ሃሳቦች ቀላል፣ በቀላሉም ሊፈበረኩ እና ከአንዱ አማኝ ወደ ሌላው አማኝ ሊተላለፉ የሚችሉ መሆን አለባቸው።

**ሁሉም አማኝ የክርስትናን መሰረታዊ ነገሮች ማወቅ አለበት፡**

- ሁሉም አማኝ ወንጌልን ለማብሰር፣ ሌሎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ እና ህብረት ለመጀመር ብቁ እንዲሆን መታጠቅ አለበት።

**እኔ ልባዛ የሚገባኝ ደቀ መዝሙር ነኝ?**

- ሁል ጊዜ ሁሉን ማባዛት ጥሩ ላይሆን ይችላል፡ ለምሳሌ የካንሰር መባዛት።
    - መጥፎ ምሳሌነት ያላቸውን ደቀ መዛሙርትን ማባዛት አንፈልግም።

- የአብርሃም ምሳሌ
    - አብርሃም ፍፁም ሰው አልነበረም ነገር ግን እግዚአብሔር ታዛዥነቱን አይቶ መረጠው።

- አ.ስ.ዋ.መ. [አፋጣኝ , ስር-ነቀል, ዋጋ የሚያስከፍል, መታዘዝ]

**የማባዛት ጠቀሜታ፡**

- እኛ ብቻችን ሁሉንም ሰው መድረስ አንችልም።
    - ደቀ መዛሙርትን የሚያፈሩ ደቀ መዛሙርት ማፍራት አለብን።
    - ሌሎች ህብረቶችን የሚጀምሩ ህብረቶች መጀመር አለብን።
- የ2-2-2 መርሆ [2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡2]
-



# ለምን? ማን? እንዴት?

ነባር አማኞችን ወይንም አዲሶችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ስትጀምሩ የመጀመሪያው ትምህርት ይህ ነው።

**ለምን እግዚአብሔር እኛን አዳረን?** ስለሚወድደን [የዮሐንስ ወንጌል 3፤16-18]። ይህን የፍቅሩን እና የምህረቱን መልካም ዜና ለሌሎች እንድናበስር እግዚአብሔር ይፈልጋል። ”4ቱን ትዕዛዛት” እና/ወይም “4ቱን ጥሪዎች” እንደሚከተለው ተመልከቱ

**4ቱ ትዕዛዛት** [የማቴዎስ ወንጌል 28፡ 19-20]

1. ሂዱ
2. ደቀ መዛሙርት አድርጉ
3. አጥምቁ
4. ትዕዛዛትን እንዲጠብቁ አስተምሯቸው

**4ቱ ጥሪዎች**

1. ከላይ የመጣ ጥሪ: የማርቆስ ወንጌል 16፤15
2. ከታች የመጣ ጥሪ: የሉቃስ ወንጌል 16፡ 27-28
3. ከውስጥ የወጣ ጥሪ: 1 ቆሮንቶስ 9፤16-17
4. ከውጭ የሆነ ጥሪ: የሐዋርያት ሥራ 16፡ 9

## ይህን የምሥራች ለማን ነው የምናበስረው?

በዙሪያችሁ ላሉት፤ በሌላ አባባል ፡ ለጓደኞቻችሁ፣ ለቤተሰቦቻችሁ፣ ለዘመዶቻችሁ፣ ለስራ ባልደረቦቻችሁ፣ ለጎረቤቶቻችሁ እና ለምታውቋቸው እና ግንኙነት ላላችሁ ሁሉ ነው።

- **ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሌላቸውን 20 ሰዎችን ባዶ ወረቀት ላይ ዘርዝሩ።** ይህን የስም ዝርዝር ይዛችሁ በፀሎት ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ፤ በሚቀጥለው ሳምንት የእራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔርን ታሪክ የምትነግሯቸውን 5 ሰዎች እንዲያመላክታችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት[የ 100 ሰዎችን ዝርዝር ደግሞ በትምህርት 3 ላይ ተጠቀሙ]።

**ይህን የምስራች እንዴት ነው የምናበስረው?** የእራሳችሁን ታሪክ የእግዚአብሔርን ታሪክ ለመንገር እንዲረዳችሁ እንደ መግቢያ ተጠቀሙት።

- ከሦስት ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የራሳችሁን ታሪክ ማካፈል:
  - ኢየሱስን ከመከተላችሁ **በፊት** ያለውን ታሪካችሁን ማካፈል።
  - **ለምን** ኢየሱስን መከተል እንደመረጣችሁ አካፍሉ።
  - ኢየሱስን ከተከተላችሁት **በኋላ** ያለውን ህይወት እና እርሱ በህይወታችሁ ያመጣውን ለውጥ
  - ? በታሪካችሁ መጨረሻም ወደ እግዚአብሔር ታሪክ ሊመራችሁ እንዲችል የሰዎችን **ምላሽ** ጠይቁ።
- **የእግዚአብሔርን ታሪክ** ለመናገር ብዙ ዘዴዎች አሉ። አንዱም ከታች እንደሚታየው 3ቱ ሳይክሎች ተብሎ የሚጠራው ነው።



# በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎች ዝርዝር

የጓደኞቻችሁን፣ የስራ ባልደረባዎቻችሁን፣ የጎረቤቶቻችሁን እና የዘመዶቻችሁን ስም ዝርዝር ጻፉ። ላላመኑት ወይም ደግሞ አቋማቸው ለማይታወቀው ፤ የራሳችሁን እና የእግዚአብሔርን ታሪክ አካፍሏቸው ወይም ወደ ህብረታችሁ እንዲመጡ ጋብዟቸው።

ለአማኞች ደግሞ ለምን? ለማን? እንዴት? የሚለውን ትምህርት እያካፈላችኋቸው ህብረት ደግሞ እንዲጀምሩ ገፋፏቸው። እናንተ እየተማራችኋቸው ያለውን የመርጃ መሣሪያዎችን እንዲጠቀሙ አበረታቷቸው በዚህ የመማር ሂደት ውስጥ በቅርብ ሆናችሁ ለመርዳት ፍቃደኞች መሆናችሁን አሳውቋቸው። በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎች ዝርዝር የሚለውን ቅፅ እንዲሞሉ አድርጓቸው[ የ20 ወይም የ100 ሰዎች ዝርዝር] የተዘረዘሩትን በቅርበት ተከታተሉ።

**ልምምድ: ክርስቲያን ያልሆኑ 20 ሰዎችን ዘርዝሩ** [ወይም 100 ክርስቲያኖችን/ክርስቲያን ያልሆኑትን ዘርዝሩ].

| | ስም | ክርስቲያን | ክርስቲያን ያልሆኑ | የማይታወቅ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 2. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 3. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 4. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 5. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 6. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 7. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 8. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 9. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 10. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 11. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 12. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 13. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 14. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 15. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 16. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 17. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 18. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 19. | ______________________ | ☐ | ☐ | ☐ |

# የራሳችሁ ታሪክ

**እግዚአብሔር በህይወታችሁ ውስጥ ምን እንዳደረገ ማካፈል**
የራሳችሁን ታሪክ እንደ መግቢያ ተናግራችሁ ለማታውቁት ሰው የእግዚአብሔርን ታሪክ ለማስተዋወቅ ከፈለጋችሁ በሦስት ታሪኮች ከፋፍሎ ማሰቡ ይረዳችኋል፡ የእነርሱ ታሪክ፣ የእናንተ ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ።

**የእነርሱ ታሪክ**፡ የምትነግሯቸውን የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔርን ታሪክ በሚረዱት መልኩ እና በራሳቸው አውድ(ንፅረተ- አለም)ለማቅረብ እንዲረዳችሁ የእነርሱን የመንፈሳዊ ህይወት ጉዞአቸውን መጀመሪያ እንዲያካፍሉ እድል ስጡአቸው።

**የራሳችሁ ታሪክ**፡ የራሳችሁን ታሪክ እንዴት በሦስት ደቂቃ ውስጥ ሦስት ቦታ ከፍላቹ መናገር እንደምትችሉ አስቡ፡

- ኢየሱስን ከመከተላችሁ **በፊት** ያለውን ታሪካችሁን ማካፈል።
- **ለምን** ኢየሱስን መከተል እንደመረጣችሁ አካፍሉ።
- ኢየሱስን ከተከተላችሁት **በኃላ** ያለውን ህይወት እና እርሱ በህይወታችሁ ያመጣውን ለውጥ
- በታሪካችሁ መጨረሻም ወደ እግዚአብሔር ታሪክ ሊመራችሁ እንዲችል የሰዎችን **ምላሽ** ጠይቁ።

**ማስታወሻ**፡ ታሪካችሁን በሌላ መንገድ ለመናገር ከፈለጋችሁ እንዴት እግዚአብሔር ህይወታችሁን እንደለወጠ፣ እንዴት እንደረዳችሁ፣ እንደፈወሳችሁ፣ ወይንም እንዴት ከአስቸጋሪው ሁኔታ እንዳወጣችሁ እና የመሳሰሉትን ታሪኮች መናገር ትችላላችሁ።

**የእግዚአብሔር ታሪክ፡** የራሳችሁን ታሪክ የምትናገሩበት ዋናው ዓላማ የእግዚአብሔርን ታሪክ እንድትናገሩ በር እንዲከፍትላችሁ ነው። የመናገር በሩ ከተከፈተላችሁ በኃላ የእግዚአብሔርን ታሪክ ተናገሩ።

**ልምምድ: የራሳችሁን ታሪክ ከታች በሚገኘው ባዶ ቦታ ላይ ከጻፋችሁ በኋላ ለሌላ ሰው ታሪካችሁን መናገር ተለማመዱ።**

# የእግዚአብሔር ታሪክ

የእግዚአብሔርን ታሪክ ለማካፈል የሚረዱ ብዙ መንገዶች አሉ (ወንጌል).  አንድ ምርጥ መንገድ አለ ማለት አንችልም። ምክኒያቱም ለአንዱ ምርጥ መንገድ ነው ያልነው ለሌላው ግን የተለየ ንፅረተ-ዓለም፣ የተለየ የሕይወት ልምምድ፣ የተለየ ባህል/ሃይማኖት ላለው ሰው የሚመረጥ ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በቀላሉ ለተለያዩ ንፅረተ ዓለሞች ሊሆን የሚችል ጠቅለል ያለ የእግዚአብሔር ታሪክ  ከፍጥረት እስከ ፍርድ ቀን ያለውን የሚተርክ አቀራረብ መጠቀም ይኖርብናል። ሌላ ከዚህ የሚሻል መንገድ ከሌላችሁ በዚህ አቀራረብ መሰረት መጀመሩ ጥሩ ነው።

## ከፍጥረት እስከ ፍርድ ቀን ያሉ ታሪኮች

እሱ እየገዛ ነው

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዓለምን ውብ እና እንከን የለሽ አድርጎ ፈጠረ። ሰውንም ከቤተሰቡ አንዱ አድርጎ ፈጠረው። ሰው ግን በእግዚአብሔር ላይ አመፀ ፤ ኃጢአትንም አደረገ መከራንም ወደ ምድር አመጣ። በዚህ ምክኒያት ሰው ከእግዚአብሔር ቤተሰብነት ወጣ።

መጣ

እግዚአብሔርም ሰውን መልሶ ወደ ቤተሰብነት እንዲያመጣ ልጁን ኢየሱስን ወደ ዓለም ላከው። ኢየሱስም በዓለም ሳለ ፍፁም የሆነ ህይወትን ኖረ፣ ሰዎችንም ስለ እግዚአብሔር አስተማረ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ሃይል ለመግለጥም ድንቅና ተአምራቶችን አደረገ፣ ብዙ ሰዎችንም ከበሽታቸው ፈወሳቸው።

ሞተ

ኢየሱስ ያለ ምንም ነቀፌታ ቢኖርም እና መሞት ባይገባውም፡ የኃጢአታችን ክፍያ ይሆን ዘንድ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞትን መረጠ።

ከሞት ተነሳ

ተቀበረ። እግዚአብሔርም የኢየሱስን መስዋዕትነት እና የኃጢአት ክፍያነቱን አየ፡ በሦስተኛውም ቀን ኢየሱስን ከሙታን በማስነሳት ክፍያውን መቀበሉን በማረጋገጫ አሳየ። እኛም አሁን ኢየሱስን እንደ ጌታችን (እንደ አምላካችን) ብንቀበለው፣ ከኃጢአታችንም ብንመለስ እና አድነን ብለን እግዚአብሔርን ብንለምን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት እንመለሳለን እርሱም መንፈስ ቅዱስን በውስጣችን እንዲኖር ይሰጠናል።

አረገ

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ለአርባ ቀናት በምድር ላይ ቆየ። ተከታዮቹንም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎችን የእርሱ ተከታይ እንዲያደርጉ እና የእግዚአብሔርን ቤተሰብ እንዲቀላቀሉ ማምጣት እንዳለባቸው ያስተምራቸው ነበር። ከዚያም ተከታዮቹ እያዩት ወደ ሰማይ ተወሰደ።

ተመልሶም ይመጣል

ወደ ፊትም ተመልሶ ጠላቶቹን እና የማይከተሉትን ይቀጣል፡ ከቤተሰቡም ጋር ለዘለዓለም ሊነግስ ይመጣል።

# የ3ቱ ሳይክሎች ዘዴ




## እነዚህን 3ቱን ሳይክሎች ስንስል የምንለው ይህ ነው፡

እኛ የምንኖረው በወደቀው ዓለም ውስጥ ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ ብዙ ስቃይ አለ፡ ይህን ለማየት ደግሞ ብዙም ከባድ አይደለም በበሽታ፣ በጥፋት፣ በጦርነት፣ ያሉ የተለያዩ ቤተሰቦች አፍንጫችን ስር ናቸው። ይህ መከራ ግን የእግዚአብሔር የመጀመሪያው እቅድ አልነበረም። እግዚአብሔር ለህይወታችን በጎ እና ፍፁም የሆነ እቅድ አለው። ወደዚህ ውድቀት ግን እራሳችንን ያስገባነው መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት በሚለው መንገድ ነው። ኃጢአት ማለት እግዚአብሔር ያቀደልንን መንገድ ትተን ወደ ውድቀት የሚያመራውን የራሳችንን መንገድ ስንከተል ነው። ይህ ውድቀት ወደ ሞት ይመራናል፡ ይህ ሞት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለዓለም ያለያየናል። እግዚአብሔር ግን በዚህ ውድቀት ውስጥ እንድንቀይ አይፈልግም።

ስለዚህ መውጫን አዘጋጀልን፡ ያ የመውጫው መንገድ ደግሞ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ መጥቶ ወደ ውድቀታችን ገባ፡ ለዚህ ውድቀታችን የሚገባን የነበረውን ሞትንም ለእኛ ሲል ወስዶ በላዩ ላይ አደረገው ስለእኛ እራሱን ለሞት ሰጠ። ከሦስት ቀንም በኋላ፡ ከሞት ተነሳ ከውድቀትም መውጫን አዘጋጀ። ሰዎች ከዚህ ውድቀት ለመውጣት ብዙ ነገርን ይሞክራሉ ለምሳሌ : ሃይማኖት፣ ስኬት፣ ገንዘብ፣ ትምህርት፣ ሃሽሽ ወይም መጠጥ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች መፍትሄ አይደሉም። አንዱ እና ብቸኛው መፍትሄ ካለንበት ነገር የሚያወጣን ኢየሱስ ነው። ከኃጢአታችን ብንመለስ ኢየሱስ ለእኛ መሞቱን እና ከሙታን መነሳቱን ብናምን ከውድቀታችን እንወጣለን። ወደ እግዚአብሔርም ቤተሰብነት እንመለሳለ፤ የእርሱንም ለእኛ ያለውን ፍፁም የሆነውን እቅድ እንከተላለን። ከዚህም በበለጠ ልክ ኢየሱስ ወደ እኛ ተልኮ እንደመጣ እኛም ደግሞ ሌሎችን ወደ ኢየሱስ መርተን ከወደቀው ዓለም እንዲወጡና እግዚአብሔር ወዳሰበላቸው መልካም እቅድ እንዲገቡ ማድረግ ይኖርብናል።

በዚህ አለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ፡ የእግዚአብሔርን ሃሳብ እየተከተሉ የሚኖሩ እና በውድቀት ውስጥ ያሉ። እኛ ራሳችንን መጠየቅ ያለብን "እኛስ የት ነን?"። እሺ፡ የት ያላችሁ ይመስላችኋል?

**"የ3ቱ ሳይክሎች" ቪዲዮ**: www.vimeo.com/happybiglife/3circles

**ልምምድ:** ከታች ባለው ክፍት ቦታ ላይ “ከፍጥረት እስከ ፍርድ ቀን”የሚባለውን ወይንም የ”3ቱ ሳይክሎች” የወንጌል መናገሪያ ዘዴ ስዕል ሳሉ።

---

**ልምምድ:** ከታች ባለው ክፍት ቦታ ላይ “ከፍጥረት እስከ ፍርድ ቀን”የሚባለውን ወይንም የ”3ቱ ሳይክሎች” የወንጌል መናገሪያ ዘዴ ስዕል ሳሉ።

# የሰላም ሰዎች

የምንባብ ክፍሎች - *የሉቃስ ወንጌል 10፥1-11 አንብ [የማቴዎስ ወንጌል 10፥5-14 በተጨማሪ አንብቡ]*

**የሰላም ሰው ባህሪያት:የተላከው የሚያደርገው ነገር:**

*የሉቃስ ወንጌል* **10:**

V. 5 - በሩን ይከፍትላችኋል
V. 6 - ባርኮታችሁን ይቀበላል እናንተንም ለመስማት ፍላጎቱን ያሳያችኋል

V. 7 - የቤቱን በር ይከፍትላችኋል/ያስተናግዳችኋል
V. 7 - በዚያ ቤትም እንድትቀመጡ/እንድትቆዩ ይጋብዛችኋል



*የሉቃስ ወንጌል* **10:**

V. 1 - ሁለት ሁለት ሆኖ መሄድን ይመርጣል
V. 2 - ለመከሩ ሰራተኞች ይጸልያል
V. 3 - በሚያስፈራ ነገር ውስጥ/በተኩሎች መካከልይሄዳል
V. 4 - ኮረጆ ወይም ከረጢት አይዝም
V. 4 - ጊዜ አያቃጥልም
V. 5 - ሰላምታ ይሰጣል
V. 6 - አሉታዊ ምላሽ ካገኘ፥ ባርኮቱን ይሰጣል
V. 7 - ከእነርሱም ጋር ህብረት ያደርጋል
V. 9 - ለታመሙት ፈውስን ከእግዚአብሔር ይጠይቃል
V. 9 - ያገለግላቸዋል
V. 9 – "የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች" እያለያውጃል
V. 10 - መልካም ምላሽ ግን ካላገኛችሁ፥ ወደ አደባባይ  ወጥታችሁ አውጁ እና ከዚያ ከተማውጡ

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ወደሚልካችሁ ቦታ ሂዱ፤ ለተጨማሪ የመከሩ ሰራተኞች ጸልዩ።
- ወደ አንድ ቦታ ወይም ስፍራ ስትገቡ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ተናገሩ/አውጁ።
- ጊዜን በከንቱ አታቃጥሉ፤ በብልሃት ጠይቁ።
- የሰላም ሰውን ጎብኙ፥ ከተቻለም እነርሱን እና ቤተሰባቸውን አሳትፉአቸው።
- ሰላምታ ስጡ፤ አስፈላጊውን መንፈሳዊ ጥያቄዎችን ጠይቁ።
- አዎንታዊ መልስ ካገኛችሁ፥ ባርኳቸው እና ወንጌልን ለመንገር የሚረዱአችሁን ጥያቄዎች ጠይቋቸው።
- ከእነዚህ ከተመረጡት ሰዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጊዜ አሳልፉ፤ በጥንቃቄ/በብልሃት ህብረት አድርጉ።
- የራሳችሁን ምስክርነት፣ ወንጌልን እና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በመናገር አገልግሉአቸው።
- ሁልጊዜም በርቱ እውነተኛም ሁኑ።
- መልካም ምላሽ ከሌለ ግን፥ በአደባባይ አውጁ እና አካባቢውን ለቃችሁ ሂዱ።

**የሰላምን ሰው ለማግኘት የሚረዱን መለኪያዎች**

- እንግዳ ተቀባይ።  ለመንፈሳዊ ነገር ረሃብ ያለው
- ሃሳብን ከሌላ ሰው ለመስማት የሚጠይቁ[የራሳቸውን ሃሳብ የሚናገሩ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችንም ለመስማት ዝግጁ የሆኑ]
- መጽሐፍ ቅዱስን በጋራ ለማጥናት ቤተሰባቸውን፣ ህብረተሰቡን እና ህብረቱን ለመሰብሰብ ፍቃደኛ የሆኑ።

**የሰላም ሰዎችን ፈልጉ:** የሰላም ሰዎች ለመንፈሳዊ ነገር ፍላጎት ያላቸው እና ቤታቸውንም ለእናንተ የሚከፍቱ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ጓደኞቻቸውን እና ቤተሰባቸውን የሚሰበስቡ እና እናንተም ህብረት እንድታደርጉበት ቤታቸውን የሚሰጡ ናቸው።

**የሰላም ህብረቶችን ፈልጉ:** በተለያየ መልኩ ያሉትን ቡድኖችን (ለምሳሌ፦ የስፖርት ቡድን፣ የሴቶች ወይም የወንዶች ቡድን፣ የሐይማኖት ቡድን የመሳሰሉትን) ፈልጉና ወደ ህብረት ለውጧቸው።

# የመጀመሪያው የህብረት ትምህርት

በሚቀጥለው ገፅ ህብረቱ ሲገናኝ የሚጠቀመው የ3 ክፍል ቅፅ ይገኛል፡፡ ከበታች የራሳችሁን ማስታወሻ ፃፉ፡

**ተጠያቂነት ዋናው እና ቁልፉ ነው [ክፍል 1]**

- ታዛዥ የሆኑ ደቀ መዛሙርት ማየት ከፈለጋችሁ፣ ለምታስተምሩአቸው ነገር ተጠያቂ አድርጓቸው፡፡
- ሰዎች በተጠያቂነት ስሜት ሆነው እምነታቸውን እንዲሰብኩ፣ በየሳምንቱ የተማሩትን አክብረው በተግባር ላይ እንዲያውሉ እና ለሌሎችም እንዲያስተላልፉት ከተፈለገ፣ ሦስት ሦስተኛ (3/3) የተባለውን ሂደት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

**የስህተት ትምህርት እንዳያስተምሩ ህብረቶችን እንዴት መጠበቅ እንችላለን?**

- አስተውሉ፣ መጋቢ ያላቸው በህንፃ ውስጥ የሚገኙ ቤተክርስቲያናት እንኳ በስህተት ትምህርት ይጠቃሉ፡፡
- የሐዋሪያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኖችም እንኳ ሳይቀሩ በስህተት ትምህርት ተጠቂ ነበሩ፣ ከዚህም የተነሳ 1ኛ እና 2ኛ ቆሮንቶስን እና ገላቲያን ለመፃፍ ተገደደ፡፡ ስህተት ትምህርት የማይቀር ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ እኛም ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡
- ህብረታችሁ በከተማ ደረጃ በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ የማስተማር ፀጋ ያላቸውን መሪዎች በመጋበዝ በስህተት ትምህርት ምክኒያት የመጡትን ችግሮች እንዲፈቱላችሁ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡
- አማኞች ማወቅ የሚገባቸውን ዕውቀት በሙሉ በአንዴ አያገኙትም፡፡ መጀመሪያ የተሳሳተው ስነ መለኮት ትምህርት ያገኛቸዋል በሂደት ግን የተማራችሁትን ዘዴ በመጠቀም እየጠራ እና እየተስተካከለ ይመጣል፡፡




**የ3/3ኛ ቅፅን በሚመች መልኩ ማስተካከል**

- የምትጠይቁትን ጥያቄዎች ለክርስቲያን ወይም ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች እንደ አስፈላጊነቱ መቀየር ትችላላችሁ፣ ነገር ግን የ3/3ኛውን ሂደት መከተልን አትርሱ፡፡
- ክርስቲያን ላልሆኑት የ3/3ኛውን ሂደት የምትጠቀሙበት የህብረት ቅፅ በመፅሐፉ ጀርባ በሚገኘው ተጨማሪ መረጃ ላይ ታገኙታላችሁ፡፡

**ልምምድ፡ የማርቆስ ወንጌል 5፥1-20ን አንብቡ እና ህብረት ማድረግን ተለማመዱ፡፡**

# የህብረት መሰብሰቢያ ቅፅ

አንድ ህብረት ሲሰበሰብ ከታች የሚገኘውን ሦስት ክፍል ያለውን (3/3) ሂደት ይጠቀማል።

## ወደ ኋላ ተመልከት

**መተሳሰብ እና አምልኮ፣** አብራችሁ ማዕድ ቁረሱ። ሁሉም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነበር? በችግር ላይ ያሉ ካሉ ጸልዩላቸው፣ ወደ ኋላም ቀረት ብላችሁ ተንከባከቧቸው። የተለያዩ እግዚአብሔር ለህብረታችሁ የሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በመጠቀም እግዚአብሔርን በጸሎት እና በዝማሬ አምልኩት።

**ጠየቅ [የማይዘለል]**

- *የተማራችሁትን እንዴት **ተገበራችሁት?***
- *የተማራችሁትን ትምህርት ማንን **አሰለጠናችሁ?***
- *የራሳችሁን ወይም የእግዚአብሔርን ታሪክ ለማን **ተናገራችሁ?***

**ራዕይ [የማይዘለል]** ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ታሪክ ወይም የግል ታሪካችሁን ተናገሩ፣ ወይም ስለ ኢየሱስ ለሌሎች እንድትናገሩ የሚያበረታታ መዝሙር ዘምሩ፣ አዲስ ህብረት ጀምሩ እና ሌሎችም ይህን እንዲያደርጉ እርዷቸው። ወይም ለመጀመር የሚረዱአችሁን እዚህ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱን ተጠቀሙ: የማቴዎስ ወንጌል 28፡18-20፣ የሉቃስ ወንጌል 10፡1-11፣ የሐዋሪያት ሥራ 1፡8፣

---

## ወደላይ ተመልከቱ

**ጸልዩ።** አጠር እና ቀለል አድርጋችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ። የሳምንቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እንዲያስተምራችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

**ብቡ እና ተወያዩ።** የዚህን ሳምንት ምንባብ አንብቡ።

- *ከዚህ ክፍል ውስጥ **የወደዳችሁት** ምንድን ነው?*
- *ከዚህ ክፍል **እራሳችሁን እንድትወቅሱ/እንድታስቡ** ያደረጋችሁ ምንድን ነው?*

**የዚህን ሳምንት ምንባብ ደግማችሁ አንብቡ።**

- *ይህ ምንባብ ስለ **እግዚአብሔር** ምን ያስተምራል?*
- *ይህ ምንባብ ስለ **ሰዎች** ምን ያስተምራል?*

---

## ወደፊት ተመልከቱ

**ጸልዩ፣ አድምጡ እና ቃል ግቡ [የማይዘለል]** በህብረት ውስጥ ያሉ ሁሉ ከታች የሚገኙትን ጥያቄዎች እንዴት መመለስ እንዳለባቸው እንዲያሳያቸው ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ። እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድታደርጉ ከነገራችሁ፣ ቃል በመግባት የተናገራችሁን ፃፉ። ከጸለያችሁም በኋላ ለህብረቱ ተናገሩ/አካፍሉ።

1. *ይህን የንባብ ክፍል እንዴት **ትተገብሩታላችሁ**?*
2. *በዚህ ምንባብ መሰረት ማንን **ታሰለጥናላችሁ**?*
3. *የእግዚአብሔር ወይም የራሳችሁን ታሪክ ለማን **ትናገራላችሁ**?*

**ልምምድ [የማይዘለል]** በጥያቄ 1፣ 2 ወይም 3 ላይ ለመፈፀም ቃል የገባችሁትን ሁለት ወይም ሦስት በመሆን እርስ በእርስ ተለማመዱ። ለምሳሌ፦ አዳጋች ንግግሮችን ወይም ፈተና ሲያጋጥማችሁ በማስመሰል ድራማ ስሩ፣ ወንጌልን መስበክ ወይንም ዛሬ የተማራችሁትን ለሌሎች ማስተማርን ተለማመዱ። ይህን አድርጋችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ከባልደረባችሁ ጋር ሆናችሁ እግዚአብሔር በዚህ ሳምንት ስለ ኢየሱስ ሊሰሙ ያሉትን ሰዎች ልብ እንዲያዘጋጅ ጸልዩ። የገባችሁትን ቃል እንድትፈፅሙ እግዚአብሔር አቅም እንዲሰጣችሁ ጠይቁት።

# የህብረት ስብሰባ መርህዎች

**የተመጠነ**

በህብረት ውስጥ ያሉ ሰዎች ቁጥራቸውን የተመጠነ አድርጉት። ህብረቶችን ስትመሰርቱ ቀድሞ ያላችሁን ግንኙነት በመጠቀም በምታውቋቸውን እና እርስ በእርስ በሚተዋወቁ ሰዎች ጀምሩ። እነዚህ ሰዎች ከዚህ በፊት የሚሰበሰቡበት ስፍራ እቤታቸው፣ ካፌ ወይም ከዛፍ ስር ከሆነ በዛው ስፍራ መሰብሰብን ቀጥሉ። ሰፊ ህብረት ኖሯችሁ ነገር ግን ትንሽ ጊዜ ከሆነ ያላችሁ 3፣ 4፣ ወይም 5 ሰዎችን የያዙ ትንንሽ ህብረቶችን መስርቱ።

**ሁሉም ሰው ማደግን በራሱ ይማራል።**

በህብረት ውስጥ ያለ ሁሉም ሰው የሚከተሉትን በራሱ ካደረገ ማደግን ይማራል፡

1. ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ተናገሩ
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ተማሩ
3. ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ፣ እርሱንም አድምጡት
4. ሌሎች አማኞችን እርዷቸው አበረታቷቸውም
5. ስደትን እና መከራን በድፍረት ተጋፈጧቸው

**ሁሉንም ደቀ መዝሙር የማድረግ ብቃት እንዳላቸው አስቧቸው**

ኢየሱስን ከማመናቸው በፊትም ሆነ በኋላ፣ ሁሉም ደቀ መዝሙር የማድረግ ብቃት እንዳላቸው ተመልከቱ። በአብዛኛው መሪዎች የትምህርት እድል ያላገኙ እና የማይከፈላቸው ናቸው።

**ታዘዙ እና አሰልጥኑ**

ህብረቱ ዕውቀት ላይ ብቻ ሳይሆን መታዘዝም ላይ የተመሰረተ ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጽሐፍ ቅዱሱን በመማር እና በመታዘዝ የኢየሱስ ተከታይ ሁኑ። በእያንዳንዱ ስብሰባችሁ ላይ ለመፈፀም ቃል የምትገቡትን ግልፅ እና ውስን አድርጉት፣ በሚቀጥለውም ስብሰባችሁ ላይ መልሳችሁ እዩአቸው። ሌሎችን እንዴት መማር እና መታዘዝ እንደሚችሉ በማሰልጠን ሰዎችን የሚያጠምዱ ሁኑ። ይህ ሁኔታ ኢየሱስን መውደድ ማለት እርሱን መታዘዝ እንደሆነ የሚያሳይ ግንዛቤን ይፈጥራል።

**በማማከር ውስጥ እና በማብዛት ውስጥ የሚፈጠሩ አዲስ ህብረቶች**

ትልቅ ህብረቶችን ከመጀመር ይልቅ ትንንሽ ህብረቶችን ለመጀመር አቅዱ። አዳዲስ ህብረቶችን የሚጀምሩ አዳዲስ መሪዎች አግኙ፣ሌሎችን እንዲያሰለጥኑ አሰልጥኗቸው። ቀጣይነት ላለው ስልጠና እና ተጠያቂነት እያንዳንዳቸውን አቅራኟቸው። ሌሎች ህብረት እንዲጀምሩ ም.እ.ማ.መ. (ምሳሌ፣ እርዳታ፣ ማየት፣ ልቀቅ) በመጠቀም እርዷቸው።

**ተወያዩና አዲስ እውቀትን አዳብሩ**

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አተኩሩ። እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንዲረዳ የሚረዳው መንፈስ ቅዱስ ላይ እምነት ይኑራችሁ። ከመስበክ ይልቅ ውይይቱን ጥያቄ በመጠየቅ ምሩት፣ ሁሉም ሰው እንዲሳተፍ እድል ስጡ።

# ጉዞውን ጀምሩ፡ የመጀመሪያዎቹ 8 ስብሰባዎች

**እያንዳንዱን ትምህርቶች ሁሉም አማኞች ማወቅ፣ ማድረግ/መታዘዝ እና ለሌሎች ማስተላለፍ ያለባቸው መሰረታዊ ትምህርቶች እንደሆኑ ተገንዘቡ። ከትምህርቱ ጋር ለመዋሃድ ከአንድ ሳምንት በላይ ከወሰደባችሁ ምንም አይደል። ይህ የጉዞ መጀመሪያ የሚደረገው ከአዳዲስ ክርስቲያኖች ጋር እንዲሁም ከዚህ በፊት ይህን አይነት ህብረት አድርገው ከማያውቁ ነባር ክርስቲያኖች ጋር ነው።**
የልምምዱ ክፍል የተዘጋጀው 8ቱን የትምህርት ክፍል አስቀድሞ በማሰብ ነው። የግል ተግባር እና ልምምድ የሚጀምረው በሚቀጥሉት ስብሰባዎች ነው። በተጨማሪም፣ አዲስ አማኝ በዙሪያው ያለውን የግል ግንኙነት ተጠቅሞ ህብረትን መመስረት ካልቻለ፣ የጉዞ መጀመሪያውን የአንድ ለአንድ የደቀ መዝሙር ትምህርት ተጠቅማችሁ በማስተማር ወደ ነባር ህብረት ትቀላቀሉታላችሁ።

## [1] የራሳችሁን ታሪክ ተናገሩ

**ወደላይ ተመልከቱ**: የማርቆስ ወንጌል 5፥1-20። በተለይ ከቁጥር 18 እስከ 20 ያለውን ክፍል በደንብ ተመልከቱት።

**ልምምድ**: የራሳችሁን ታሪክ ተናገሩ ፡ ታሪካችሁን ለሌሎች ለመናገ አስቀድሞ መዘጋጀት እና ዝግጁ መሆንያስፈልጋል። በሦስትክክፍል ብቻ ታሪካችሁን እንዴት መናገር እንደምትችሉ ተመልከቱ፡

- **ኢየሱስን ከማግኘታችሁ በፊት ያለውን የህይወታችሁን ታሪክ ተናገሩ** - ኢየሱስን ከማግኘታችሁ በፊት ያላችሁን ጥያቄዎች [ከሞት በኋላ ምን አለ?]፣ የሚሰማችሁን ስሜት [ስቃይ፣ ብቸኝነት]ወይም የሚያታግላችሁን ነገር ግለፁ።
- **እንዴት የኢየሱስ ተከታይ ልትሆኑ እንደቻላችሁ ተናገሩ** - ስለ ኢየሱስ ንገሯቸው! ሁላችንምከእግዚአብሔር ጋር ተላልፈናል፣ ከኃጢአታችንም የተነሣ ሞት ይገባናል፤ ነገር ግን ስለ እኛ በሞተው፣በተቀበረው፣ ከሙታንም በተነሳው በኢየሱስ ስናምን ከዚህ ሞት ተርፈናል። የማይለወጠው የኢየሱስ ታሪክ ይህ ነው።
- **ኢየሱስን ከተከተላችሁት በኋላ ስላለው ህይወታችሁ ተናገሩ** - ኢየሱስ እንዴት ህይወታችሁንእንደቀየረው ንገሯቸው። ኢየሱስ ስለሰጣችሁ ደስታ፣ ሰላም እና ምህረት ተናገሩ።
- **? የሰዎችን ምላሽ ስሙ** - በታሪካችሁ መጨረሻ ሰዎች ለሰሙት ነገር ምላሻቸውን እንዲሰጡ ጊዜ መስጥት አለባችሁ። የአድማጫችሁን የመንፈሳዊ መረዳት/ፍላጎት ለማወቅ እንዲረዳችሁ ታሪካችሁን ጥያቄን በመጠየቅ ጨርሱ፡ ለምሳሌ “ይህንን ምህረት እናንተስ እንዴት እንደምታገኙት ማወቅ ትፈልጋላችሁ?” ወይም “እግዚአብሔር ህይወታችሁን እንዲለውጥ ትፈልጋላችሁ?”

**አጠር አድርጋችሁ አቅርቡት** [በ 3 ደቂቃ ወይም ከዛም ያነሰ] - ታሪካችሁ አጭር እና የሚስብ መሆን አለበት። ረዥም ሰዓት በማውራት ሰዎች እንዲሰላቹ አታድርጉ።

በቡድናችሁ ውስጥ ካለ ከአንድ ሰው ጋር ታሪካችሁንድ መናገር **ተለማመዱ**

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የእራሳችሁን እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን እንደምትናገሩ እንዲመራችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

## [2] የእግዚአብሔር ታሪክ ተናገሩ

**ወደላይ ተመልከቱ**: 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥1-8፣ ሮሜ 3፥23፣ ሮሜ 6፥23

**ልምምድ**: በህብረታችሁ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ሰዎች የፍጥረት እስከ ፍርድ ቀን ታሪክ የመናገሪያ ዘዴን ወይም 3ቱ ሳይክሎች እና ሌላ ቀለል ያለ የታሪክ መናገር ዘዴን በመጠቀም የኢየሱስን ታሪክ መናገር እንዲለማመዱ አድርጉ።

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁእንዲያሳያችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

## [3] ተከታትላችሁ አጥምዱ

**ወደላይ ተመልከቱ**: የማርቆስ ወንጌል 1፡16-20

**ልምምድ**: **በባዶ ወረቀት ላይ** እስከ 100 የሚደርስ የሰዎች ስም(ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ጎረቤቶች፣ የስራ ባልደረቦች እና የመሳሰሉትን) ዝርዝር ጻፉ። ከተዘረዘሩት ውስጥ ክርስቲያን ላልሆኑትን፣ የራሳችሁን እና የእግዚአብሔር ታሪክ ንገሯቸው። ክርስቲያን ለሆኑት ግን እንዴት ወደ ህብረታችሁ መጋበዝ እንደምትችሉ አስቡ ወይም የተማራችሁትን የደቀ መዝሙር ማድረጊያ መርጃ መሣሪያዎችን በእርጋታ አሳዩአቸው።

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

## [4] ጥምቀት

**ወደላይ ተመልከቱ**: ሮሜ 6፡3-4፤ የሐዋሪያት ሥራ 8፡26-40

**ልምምድ**: በአቅራቢያችሁ ወደ ሚገኘው ወንዝ፣ ሀይቅ፣ ወይም የመዋኛ ስፍራ ፈልጉ እና አዲስ አማኞችን ሁሉ አጥምቋቸው። ያመኑትን ሰዎች ወዲያው ማጥመቅ ልማዳችሁ አድርጉት። ስለ ጥምቀት ጠለቅ ያለ ዕውቀት እንዲኖራችሁ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን አንብቡ፡ የሐዋሪያት ሥራ 2፡37-41 ፤ 8፡5-13፤ 8፡36-38፤ 9፡10-19፤ 10፡47-48፤ 16፡13-15፤ 16፡27-34፤ የሐዋሪያት ሥራ 18፡5-9 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10-17፤ የሐዋሪያት ሥራ 19፡1-5፤ የሐዋሪያት ሥራ 22፡14-17።

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

## [5] መጽሐፍ ቅዱስ

**ወደላይ ተመልከቱ**: 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14-17

**ልምምድ**: በ3/3ኛው ስብሰባ ላይ ህብረታችሁ የተጠቀመውን ቅፅ አስታውሱ። በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነቡበት እና
የሚጸልዩበት የጥሞና ጊዜ እንዲኖራቸው እያንዳንዱን ሰው አበረታቱ።

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

## [6] ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ

**ወደላይ ተመልከቱ**: የማቴዎስ ወንጌል 6፡ 9-13

**ልምምድ**: በማቴዎስ ወንጌል 6፡ 9-13 የሚገኘውን የኢየሱስ ጸሎት በህብረታችሁ ውስጥ ጸልዩት፡ እያንዳንዱን ሰው በየቀኑ ይህን ጸሎት እንዲጸልዩ አበረታቷቸው። ይህን ጸሎት መጸለይ የምትማሩት እጃችሁን በመጠቀም ነው።

1. **መዳፍ = ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ህብረት.** መዳፋችን ለጣቶቻችን መነሻ መሰረት እንደሆነው ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ከእርሱ ጋር ላለን ህብረት መሰረታዊ ነው። *"በሰማይ*

*የምትኖር አባታችን ሆይ…” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥9]*

2. **የአውራ ጣት = አምልኮ።** የአውራ ጣታችን የሚያስታውሰን ማንኛውንም ጥያቄ እግዚአብሔርን ከመጠየቃችን በፊት እርሱን ማምለክ እንዳለብን ነው። *“…ስምህ ይቀደስ” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥9]*
3. **ጠቋሚ ጣት = መገዛት።** የሚቀጥለው ደግሞ ህይወታችንን፣ እቅዶቻችንን፣ ቤተሰቦቻችንን፣ገንዘባችንን እና ስራችንን በአጠቃላይ ሁሉ ነገራችንን ለእርሱ ማስገዛት ነው። *“መንግሥትህ ተምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣ እንዲሁም በምድር ትሁን…” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥10]*
4. **የመሃል ጣት = መጠየቅ።** ከዚያም የሚያስፈልገንን እንዲሰጠን እግዚአብሔርን እንጠይቃለን። *“የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥11]*
5. **የቀለበት ጣት = ይቅር ማለት።** አሁን ደግሞ ኃጢአታችንን እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን እንጠይቃለን፤ እኛም ደግሞ ሌሎችን ይቅር እንላለን። *“እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን።” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥12]*
6. **ትንሿ ጣት = ጥበቃ።** እግዚአብሔር ከክፉ እንዲጠብቀን እንጸልያለን። *“ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉው አድነን እንጂ…” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥13]*
7. **በድጋሚ የአውራ ጣት = አምልኮ።** ስንጀምር እግዚአብሔርን በማምለክ እንደጀመርነው አሁንም በአምልኮ እንጨርሳለን። *“መንግሥት፣ኃይል፣ ክብርም፣ ለዘለዓለሙ ያንተ ነውና፤ አሜን።” [የማቴዎስ ወንጌል 6፥13].*

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

## [7] አስጨናቂ ቀኖች

**ወደላይ ተመልከቱ:** የሐዋሪያት ሥራ 5፥17-42፤ የማቴዎስ ወንጌል 5፥43-44

**ልምምድ:** ኢየሱስን በማመናችሁ የደረሰባችሁን አስጨናቂ ነገሮች ለህብረቱ ተናገሩ፤ እነዚያን ከባድ ጊዜያት ልክ ኢየሱስ እንዳስተማረው በድፍረት እና በፍቅር ምላሽ እየሰጣችሁ እንዴት እንደምታልፏቸው በድራማ መልክ አሳዩ። እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ጸልዩላቸው። ታሪካቸውን ተናግረው ሲጨርሱ ለእያንዳንዱ ሰው ጸልዩላቸው።

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

## [8] የተሟላ እና ራሱን የቻለ ህብረት መሆን

**ዐደላይ ተመልከቱ:** የሐዋሪያት ሥራ 2፥42-47፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥23-34

**ልምምድ:** ህብረታችሁ ልክ ከላይ እንደተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ህብረቶችንእንዲመስል ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ተወያዩ። እንደ ህብረት በባዶ ወረቀት ላይ በነጠብጣብ ክብ ምስል ሳሉ፣ ይህም የእናንተን ህብረት እንዲያመለክት ነው። ከክቡም ላይ 3 ቁጥሮችን ጻፉ፡ አንዱ ቁጥር በቋሚነት በህብረት ውስጥ የሚመጡትን (የሆነ ስዕል ለጥፉ)፣ ሌላው ቁጥር ደግሞ በኢየሱስ የሚያምኑትን ያሳያል (የመስቀል ስዕል አድርጉበት) እናም የመጨረሻ ቁጥር የተጠመቁትን ያሳያል (የውሃ ስዕል)። ህብረታችሁ ቋሚ ህብረት ለመሆን ቃል የገባ ከሆነ ነጠብጣቡን ክብ ድፍን መስመር አድርጉት። ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነገሮች በህብረታችሁ ውስጥ የምታደርጉት ከሆነ በክቡ ውስጥ በስዕል መልክ አስቀምጧቸው፤ እነዚህን ነገሮች ግን በህብረታችሁ ውስጥ የማታደርጉ ከሆነ ወይንም ሌላ ከህብረታችሁ ውጭ የሆነ ሰው እንዲያደርጉላችሁ የምትጠብቁ ከሆነ ከክቡ ውጪ በስዕል መልክ አስቀምጧቸው።

1. በህብረት ለመሆን ቃል የገቡ ከሆነ ፡ በነጠብጣቡ ፈንታ ድፍን መስመር።
2. ጥምቀ፡
3. መጽሐፍ ቅዱስ
4. ኢየሱስን በጌታ እራት (ስጋ እና ደሙን በመውሰድ) ማስታወስ

5. የአንድነት ጊዜ
6. በመስጠት ማገልገል
7. ጸሎት
8. ምስጋና
9. ስለ ኢየሱስ ለሰዎች መናገር
10. መሪዎች



ህብረታችሁ ጤናማ እንዲሆን የሚረዳው፤ አሁን ግን የሌለው ምንድን ነው?

**ጸልዩ።** በዚህ ሳምንት የራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ ለማን መናገር እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔር ጠይቁት።

**የሚቀጥለው ወደየት ነው? አዲስ ነገርን የመረዳት ተከታታይ ክፍል** ወይም **የማጠናከሪያ ተከታታይ ክፍልን** ተመልከቱ።

# የስልጠናው ሳይክል - ም.እ.ማ.መ.



- **ምሳሌ** - እንዴት እንደሚያደርጉ በምሳሌ አሳዩአቸው [ከ2 እስከ 3 ሳምንታት]
- **እርዳታ** - እራሳቸው እንዲያደርጉት እርዱአቸው [ከ2 እስከ 3 ሳምንታት]
- **ማየት** - እራሳቸው ሲያደርጉት እዩአቸው [ከ2 እስከ 3 ዓመታት ወይንም ከዛም በላይ]
- **መልቀቅ** - ስራውን እንደሚሰሩ አምናችሁ ልቀቋቸው

**ም.እ.ማ.መ.**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የመጀመሪያ ትውልድ | **ምሳሌ** | **እርዳታ** | **ማየት** | **መልቀቅ** | | |
| ሁለተኛ ትውልድ | | **ምሳሌ** | **እርዳታ** | **ማየት** | **መልቀቅ** | |
| ሦስተኛ ትውልድ | | | **ምሳሌ** | **እርዳታ** | **ማየት መ** | **ልቀቅ** |
| አራተኛ ትውልድ | | | | **ምሳሌ** | **እርዳታ** | **ማየት** |
| **መልቀቅ** | | | | | | |

**በተመሣሣይ ጊዜ የሁለት ህብረቶች አባል መሆን፡**

- የራሳችሁን ህብረት እንደ መጀመሪያው መንፈሳዊ ቤተሰባችሁ ይሆናል
  - ከ6 እስከ 12 አዋቂዎች በህብረት ውስጥ ይገኛሉ።
  - አዲስ አማኞችን ወደዚህ ህብረት ከምታመጧቸው ይልቅ ካላቸው ግንኙነት ተነስተው አዲስ ህብረት እንዲመሰርቱ ምሳሌ አሳዩአቸው እና በሚያደርጉበትም ጊዜ እርዷቸው።

- የሚጀምሩት አዲስ ህብረት የመጀመሪያ መንፈሳዊ ቤተሰብ እንዲሆናቸው ሌሎችን ያለማቋረጥ ሁልጊዜ ትረዳላችሁ።
  - ይህንን ነው "ምሳሌ እና እርዳታ" ብለን የምንጠራው። ስለዚህ፣ ሌሎች አዲስ ህብረቶችን ምሳሌ እና እርዳታ በመስጠት እየረዳችሁ በተመሳሳይ ጊዜ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ህብረቶች ውስጥ አባል ትሆናላችሁ ማለት ነው።
  - **ነገር ግን በአንድ ጊዜ በጣም ብዙ ህብረት ከጀመራችሁ፣ የራሳቸውን ህብረት የሚጀምሩትን እንደሚገባው ምሳሌ እና እርዳታ መስጠት አትችሉም።**

**እያንዳንዱ ህብረት በአመት አንድ አዲስ ህብረት እያስጀመረ የሚበዛበት ሂደት፡**

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ ዓመት = 1 | 11ኛ ዓመት = 1,024 | 21ኛ ዓመት = 1,048,576 |
| 2ኛ ዓመት = 2 | 12ኛ ዓመት = 2,048 | 22ኛ ዓመት = 2,097,152 |
| 3ኛ ዓመት = 4 | 13 ኛ ዓመት = 4,096 | 23 ኛ ዓመት = 4,194,304 |
| 4ኛ ዓመት = 8 | 14 ኛ ዓመት = 8,192 | 24 ኛ ዓመት = 8,388,608 |
| 5ኛ ዓመት = 16 | 15ኛ ዓመት = 16,384 | 25ኛ ዓመት = 16,777,216 |
| 6ኛ ዓመት = 32 | 16 ኛ ዓመት = 32,768 | 26 ኛ ዓመት = 33,554,432 |
| 7ኛ ዓመት = 64 | 17 ኛ ዓመት= 65,536 | 27 ኛ ዓመት = 67,108,864 |
| 8ኛ ዓመት = 128 | 18 ኛ ዓመት= 131,072 | 28 ኛ ዓመት = 134,217,728 |
| 9ኛ ዓመት = 256 | 19 ኛ ዓመት = 262,144 | 29 ኛ ዓመት = 268,435,456 |
| 10ኛ ዓመት = 512 | 20 ኛ ዓመት = 524,288 | 30 ኛ ዓመት = 536,870,912 |

# ም.እ.ማ.መ. እና ህብረት የማብዛት ሁኔታዎች ማሳያ




BB ህብረት Z የተባለውን የሰላም ሰው ወደ ክርስቶስ አመጡ። Z “ለምን? ማን? እንዴት?” የሚለውን የደቀ መዝሙር ማድረጊያ ትምህርት ከወሰደ በኋላ ጓደኞቹን እና ቤተሰቡን ሰብስቦ አዲስ ህብረት ለመመስረት ችሏል።
BBዎች አሁንም የመጀመሪያ ህብረታቸው አካል ቢሆኑም Zን ምሳሌ በማሳየት እና በመርዳት አዲስ ህብረት እንዲፈጥር ሆኗል።
ከዚህ በኋላ Z በተማረው እና ባየው መሰረት ህብረትን ሲመሰርት ለመከታተል BBዎች በማየት ላይ ናቸው።

የZ ጓደኛ የሆነው M ክርስቲያን ሲሆን የZ ህብረት ለመቀላቀል ጥያቄ አቀረበ።
Zም፡ “የኔ ህብረት ሞልቷል ነገር ግን ሌላ ከጓደኞችህ እና ከቤተሰብህ የተውጣጣ አዲስ ህብረት እንድትመሰርት ልርዳህ” አለው።
ስለዚህ Z ለ M ምሳሌን አሳየው በመመስረት ሂደቱም ላይ እረዳው።
Z ይህ አዲሱ ህብረት እራሱን እስኪችል ድረስ ለ2 ወር ያህል በመርዳት ከእነርሱ ጋር ነው እንጂ የዚህ ህብረት አካል አይደለም።

QQ ከ T እና ህብረቷ ጋር ም.እ.ማ.መ.ን እየሰሩ ናቸው። ይህ ህብረት ከBB ህብረት በመነሳት 4ኛው ትውልድ ነው። እዚህ ደረጃ ከደረሳችሁ ያለጥርጥር የብዜቱ DNA እንደተዋቀረ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ።

- የሁሉም ህብረት መሪዎች በአመት ውስጥ ለተወሰኑ ጊዜያት ቀጣይነት ላለው የመሪነት እድገት እና ለስልጠና በአንድ ላይ ይሰበሰባሉ።
- ህብረቶች በየሳምንቱ ይሰበሰባሉ። የደቀ መዝሙርነት ህይወት የሚታየው በእነዚህ ጊዜያት ነው። በከተማ ወይም በክልል ደረጃ የሚገኙ ህብረቶች በሙሉ ደግሞ ክብረ በዓል ለማክበር ወይም ወንጌልን ለማሰራጨት በወር፣ በሦስት ወር ወይም በዓመት በዓል ጊዜ ይሰበሰባሉ።

# የጸሎት ጉዞ

የጸሎት ጉዞ ለብቻ ማድረግ ቢቻልም፣ በሁለት ወይም ሦስት ቡድን ቢሆን ደግሞ የተሻለ ነው። በቡድን የሚደረገው ጸሎት ጥቅሙ እግዚአብሔር ለሌሎች እንዴት እንደሚናገር ማየት እንችላለን። ይህ ደግሞ የጸሎት ሕይወታችሁን በማስፋት የእግዚአብሔርን መንገድ ወደመለየት የጠለቀ እድገት ይወስዳችኋል። በቡድን በምትጸልዩበት ጊዜ ሌሎች እየሰሙ ከጸሎታችሁ ጋር እንዲስማሙ ድምጻችሁ ከፍ ማለት አለበት። ሌላ ሰው ባለበት ለዛ ሰው ለመጸለይ ካልሆነ በቀር ብቻችሁን ስትሆኑ በፀጥታ ጸልዩ።

በጸሎት ጉዞ ላይ ስትሆኑ 4 እንዴት መጸለይ እንዳለብን የሚመሩ መንገዶች አሉ፡

1. **መቃኘት/መመልከት**: ለምሳሌ በጓሮአችን ሆነን ሳለ ሦስት ጎማ ያለው የህፃናት ሳይክል ስናይ፣ ስለ ልጆች፣ ስለ ቤተሰቦች፣ ስለ ትምህርት ቤቶች፣ ስለ መጓጓዣ እና የመሳሰሉት ነገሮች እንድንጸልይ ያነሳሳናል። እነዚህ የምናያቸው አካላዊ ቁሳዊ ነገሮች በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ስላሉ ሃሳቦች እንድናስተውል ያደርጉናል።
2. **ጥናት**: በጸሎት ጉዞአችሁ ላይ እያላችሁ አንዳንድ ወንጀል የሆኑ ነገሮች ወይም ኢፍትሃዊ ነገር ብትመለከቱ፣ ጸሎታችሁ ስለእነዚህ ነገሮች እንዲሆን ሊመራችሁ ይችላል።
3. **መገለጥ**: ስለ አንድ ጉዳይ እንድትጸልዩ የሚመራችሁ የመንፈስ ቅዱስ ጉትጎታ ወይም ምስል ልትቀበሉ ይችላል።
4. **መጽሐፍ ቅዱስ**: ቀደም ብላችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መርጣችሁ የዚያ ክፍል ጭብጥ መልዕክት የጸሎታችሁ ሃሳብ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።

ተፅእኖ የሚፈጥሩ ቦታዎች ላይ ለየት ያለ ትኩረት አድርጉ ፡

**የመንግስት ቦታዎች** ለምሳሌ ፍርድ ቤቶች
**የንግድ ቦታዎች** ለምሳሌ የገበያ መአከሎች
**የትምህርታዊ ቦታዎች** ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች
**የግንኙነት ቦታዎች** ለምሳሌ የራዲዮ ጣቢያዎች
**የመንፈሳዊ ቦታዎች** ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያን ህንፃዎች፣ መስኪዶች ወይም ቤተ መቅደሶች

በጸሎት ጉዞአችሁ ላይ ሳላችሁ ለምታገኟቸው ግለሰቦች ወይም የሰዎች ስብስብ የመጸለይ እድልን ወይም ከመንፈስ ቅዱስ የሆነን መረዳት ፈልጉ። "ስለዚህ ህብረተሰብ እየጸለይኩ/እየጸለይን ነው፣ እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉት ርዕስ አለ?"ወይም "ስለዚህ ህብረተሰብ እየጸለይኩ/እየጸለይን ነው፡ ስለምን መጸለይ እንዳለብን ልትነግሩን ትችላላችሁ?" በማለት የጸሎት ርዕስ መጠየቅ ትችላላችሁ። ምላሻቸውን ከሰማችሁ በኋላ የግላቸውን የጸሎት ርዕስ እንዲነግሯችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ፣ ከነገሯችሁ በኋላ እዛው ጋር ጸልዩላቸው። በመጸለይ ላይ እያላችሁ ጌታ ስለ ሌላ ነገራቸውም እንድትጸልዩ ከመራችሁ ጸልዩላቸው። [BLESS] የሚለውን ምዕጻረ ቃል አድርገን ለጸሎት እንዲመራን ማድረግ እንችላለን ፡

**Body ባዲ** [ጤንነት]
**Labor ሌበር** [ስራ እና ገንዘብ]
**Emotional ስሜት**[ስነ ልቦና]
**Social** ማህበራዊ [ግንኙነት]
**Spiritual መንፈሳዊ**

ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ መቅርቀራችሁ/ማሰባችሁ ሰዎችን እንዲያመሰግኑ ያደርጋቸዋል ። ያገኛችሁት ሰው ክርስቲያን ካልሆነ ምስክርነታችሁን ለመናገር፣ ወንጌልን ለመስበክ፣ ለመንፈሳዊ ጭውውት አሊያም ደግሞ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ህብረታችሁ ለመቀላቀል ወይም በቤታቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲጀምሩ ለመጋበዝ በር ከፋች ይሆንላችኋል። ያገኛችሁት ሰው ግን ክርስቲያን ከሆነ የጸሎት ጉዞው ላይ እንዲቀላቀላችሁ መጋበዝ ወይም በሌላ የደቀ መዝሙር አሰራሮች ማስታጠቅ አለባችሁ።

**ልምምድ: 2 ወይም 3 ሆናችሁ ለጸሎት ጉዞ ውጡ።**

# የመጀመሪያውን ህብረት እንዴት ትጀምራላችሁ?

**የመጀመሪያውን ህብረት፣ ባላቻሁበት ቤተ ክርስቲያን ወይም ድርጅት የደቀ መዝሙርን ማፍሪያ እንቅስቃሴን ለመጀመር ተጠቀሙት**

## ከስብሰባ በፊት

ከተማቸውን ወይም ሀገራቸውን የሚያጥለቀልቅ የደቀ መዝሙርነት እንቅስቃሴ አካል መሆን እንዴት እንደሚችሉ ራዕያቸሁን በቤተ ክርስቲያናችሁ ለሚገኙ ክርስቲያኖችን አካፍሉ። ከዛም እንደ የመጀመሪያ እነዚህን ሰዎች ሰብስባችሁ ከስር በተገለፀው ፕሮግራም መሰረት የደቀ መዝሙር ስልጣናን አሰልጥኗቸው።

## 1ኛ ሳምንት

በመጀመሪያው ለምን? ማን? እንዴት? በሚለው ትምህርት ጀምሩ። ለዚህም የሚያስፈልጋችሁ ወደ 2 ሰዓታት ያህል ነው።

## 2ኛ ሳምንት [እና ቀጣይ ሳምንታት]

የ3ቱን ክፍል ሂደቶች የሚጠቀመውን የጉዞ መጀመሪያን ተጠቅማችሁ በህብረቱ ስብሰባ አሰራር ላይ አቀናጁት። በዚህ ሳምንት የመጀመሪያውን ትምህርት ጀምሩት፣ ከዚያም ህብረታችሁ በትክክል ታሪካቸውን መናገር ከቻሉ፣ ወደ ሚቀጥለው ትምህርት ዝለቁ። ይህ ካልሆነ ግን፣ ሁሉም ሰው ታሪካቸውን መናገር እስኪችሉ ድረስ ለሚመጣው 1 ወይም 2 ሳምንታት የመጀመሪያው ትምህርት ላይ መቆየት አለባችሁ። ይህን አይነት አሰራር ተከትላችሁ በድምሩ 8 ትምህርቶችን ማጠናቀቅ ይጠበቅባችኋል።

- ትምህርት 1: የራሳችሁን ታሪክ ተናገሩ
- ትምህርት 2: የእግዚአብሔር ታሪክ ተናገሩ
- ትምህርት 3: ተከታትላችሁ አጥምዱ
- ትምህርት 4: ጥምቀት
- ትምህርት 5: መጽሐፍ ቅዱስ
- ትምህርት 6: ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ
- ትምህርት 7: አስጨናቂ ቀኖች
- ትምህርት 8: የተሟላ እና ራሱን የቻለ ህብረት መሆን

## ከአዲስ አማኞች ጋር ምን ማድረግ አለባችሁ?

አንድ ሰው ወንጌልን አምኖ ከተቀበለ፣ የመጀመሪያዎቹን ለምን? ማን? እንዴት? የሚሉትን ትምህርት ጊዜ እስከፈቀደ ድረስ መማር አለበት። ጊዜው ካልበቃ፣ ሌላ ጊዜ ለመገናኘት ቀን ቀጠሩ። አዲሶቹን አማኞች ወደ መጀመሪያው ህብረት አትመልሷቸው ። የመጀመሪያ ህብረት ውስጥ ከተቀላቀሉ፣ በሰለጠነው የህብረቱ መሪ ላይ ተማምነው ይቀመጣሉ ይህ ደግሞ መታዘዝን መሰረት ያደረገውን ደቀ መዝሙርነትን እና አዲስ መሪዎችን የማፍራት ሂደትን ይገድላል። ከዚህ ይልቅ አዲሱ አማኝ ከቻለ ያለውን ግንኙነት ተጠቅሞ ህብረት እንዲመሰርት እርዱት። አዲስ አማኙን ግን አዲስ ህብረት እንዲመሰርት ማድረግ ካልተሳካላችሁ፣የጉዞ መጀመሪያ ትምህርቱን አንድ ለ አንድ በሆነ መንገድ አስተምሯቸው አለበለዚያ ቀድሞ የነበረ ህብረት ውስጥ ቀላቅሏቸው።

# የማብዛት እና የደቀ መዝሙርነት መርህዎች

ፈጣን ወደሆነ የደቀ መዛሙርት ማብዛት ሂደት የሚመሩን መርህዎች ምንድን ናቸው?

## መርህ #1 - ሁሉም ሰው የታጠቀ/የተዘጋጀ ነው

- ሁሉም ደቀ መዝሙር ደቀ መዝሙር አድራጊ፣ ሁሉም ቤት የስልጠና ቦታ እና ሁሉም ህብረት ደግሞ የሚስዮን ድርጅት ነው።

## መርህ #2 - ሁለት ተጠያቂነት

- ከእግዚአብሔር የሰማችሁትን እና የገለጠላችሁን ነገር መታዘዝ

- ለሌሎች ማካፈል

**የዳክዬ ልጆች አይነት ደቀ መዝሙርነት: ኢየሱስ ልክ እንደ ዳክዬዎቹ እናት ነው። ሁላችንም እርሱን እየተከተልን ነው። ሌሎችን ለማስከተል ግዴታ** የጎለመሱ ዳክዬዎች መሆን አይጠበቅባችሁም. . . በአንድ ደረጃ ብቻ እነርሱን መቅደም ነው የሚኖርባችሁ።



## መርህ #3 - እያንዳንዱ ደቀ መዛሙርት ከታች በተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ እራሳቸውን ማሳደግ አለባቸው

1. በቃሉ [መጽሐፍ ቅዱስ]

2. በጸሎት

3. በአካሉ ህይወት [ከሌሎች አማኞች ጋር መገናኘት]

4. በስደት እና መከራ

## መርህ #4 - የእግዚአብሔር መንግስት ያልተገለጠበትን ፍራዎች የሚያዩ አይኖች

- በአካባቢያችሁ የምታዩት የእግዚአብሔር መንግስት የጠፋበት ቦታ የቱ ነው? እነዚህ ቦታ ላይ በምን መልኩ እና እንዴት መስራት ትጀምራላችሁ? ሁልጊዜም የእግዚአብሔር መንግስት ያልገባባቸው ቦታዎች ማየት አለብን።
- ኢየሱስ የተናቁትን፣ የተረሱትን እና የጠፉትን ይወዳል። እናንተም ሁን ብላችሁ በማስተዋል እነዚህን አይነት ሰዎች ፈልጉ።

# በጥቂቶች ላይ መዝራት

- ጊዜአችሁን የምታጠፉት ከማን ጋር ነው? ያስተማራችኋቸውን በህይወታቸው ከሚተገብሩት እና ለሌሎች ከሚያስተምሩ ጋር!
- ለመሰልጠን ፍቃደኛ የሆኑትን አሰልጥኑ፣ ግን ለፍሬው ደግሞ መከታተል ይጠይቃል።
- ለጥቂቶች የውስጣቸውን ለሚያፈሱት ለእነርሱ ውስጣችሁን አፍሱ።

# የሚያስከፍለው ዋጋ

- የደቀ መዝሙርነት መርህዎችን ብትኖሩአቸው፣ ስደት ወይም የመንፈሳዊ ውጊያ እና ስቃይ ይደርስባችኋል።
  - 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥11-12 & ሮሜ 8፥17

- እግዚአብሔር እነዚህን ጥቃቶች መዋጀት እና ለበጎ መቀየር ይችላል።
  - ሮሜ 8፥28

# እነዚህን መርሆች ማካፈል

- አሁን የተማራችሁትን በተግባር መፈጸም ከቻላችሁ በኋላ፣ ለማን ታካፍሉታላችሁ?
  - ለወጣቶች ወይም ለአዲስ አማኞች ማከፈሉ የተመረጠ ነው። ሰዎች ባረጁ ቁጥር ወይም በክርስትና በቆዩ ቁጥር አዲስ ለሆነ የደቀ መዝሙር ማድረጊያ መንገድ ክፍት የመሆን ዕድሉ የጠበበ ነው። ይህ እውነታ ለ ቤተ ክርስቲያን ሆነ ለድርጅት ይሰራል። ምክኒያቱም ድርጅቶቹ ወይም ቤተ ክርስቲያናት ባደጉ ቁጥር ወይም ብዙ እድሜን ባስቆጠሩ ቁጥር ለለውጥ ክፍት የመሆን እድሉ አናሳ ነው።
  - የሉቃስ ወንጌል 5፥ 36-39

# የመጨረሻ ሃሳቦች

- የሚባዙ ህብረቶች ላይ መስራት እንፈልጋለን። የጀመራችሁት ህብረት የማይባዛ ከሆነ፣ አሁንም ቢሆን ጨለማ ውስጥ ያበራ ብርሃን ስለሆነ ፥ አትጨነቁ! እንደገና ሞክሩ።
- ዋይን ግሬትዝኪ አንድ ጊዜ እንደተናገረው “ያልሞከርከውን ነገር 100 % ትስተዋለህ!“
  - ለመሳሳት አትፍሩ። እጃችሁ በመስራት ይቆሽሽ!

# ጴቀ መዝሙር የማድረጊያ መሣሪያዎች ማጠቃለያ

መቼ እና እንዴት እነዚህን የጴቀ መዝሙር መሣሪያ እንጠቀማለን

**ክርስቲያን ካልሆኑት ጋር ህብረቶችን ለመንፈሳዊ ጉዞ እድገት መጠቀም ይቻላል**[ለምስሳሌ፦ የመረዳት ጉዞ፣ የተስፋ ጉዞ እና የዮሐንስ ጉዞ ምልክቶች]ወይም ከመሰል ጴቀ መዛሙርት ጋር [የመረዳት ጉዞ፣ የመጀመሪያ ጉዞ፣ የማጠናከሪያ ጉዞ]። አንድ ቀጣይነት ያለው የመጀመሪያ መንፈሳዊ ሰዎች መንደር ይኑራችሁ። በራሳችሁ ቤት ወይም መገናኘት በምትፈልጉበት ቦታ መሰብሰብ ይችላሉ። በተመሳሳይ ጊዜም ጊዜያዊ በሆነ መልኩ አዲስ ህብረትን ምሳሌ ለማሳየት እና ለመርዳ ሞክሩ። ይህ ሁሉ ግን የሚሆነው እነርሱ መገናኘት በሚፈልጉበት ቦታ ነው። አዳዲስ አማኞች ከጉዞ መጀመሪያ ክፍል መጀመር አለባቸው። በነባር የክርስቶስ ተከታዮችም ቢሆኑድ ጴቀ መዝሙር ማፍራት ስልጠና ላይ  ከጉዞ መጀመሪያ ክፍል መጀመር አለባቸው።

ለምን? ማን? እንዴት? የሚሉት የትምህርት ክፍሎች ጴቀ መዝሙርነትን ለመጀመር መሰረታዊ ናቸው። ወደ ጌታ ያመጣችኋቸውን አዲስ አማኞችን ለማስተማር ይህን ትምህርት መጠቀም አለባችሁ ምክኒያቱም እምነታቸውን በሚያካፍሉበት ትክክለኛ መንገድ ለማስጀመር እና ወደ እምነት የሚያመጡትንም ጴቀ መዝሙር እንዲያደርጉ የሚረዳቸው ስለሆነ። ለነባር ክርስቲያኖችም ይህን ትምህርት እምነታቸውን እንዲያካፍሉ እና ጴቀ መዝሙር እንዲያደርጉ ስለሚረዳቸው ትምህርቱን መጠቀም አለባችሁ። ። አማኞች የቢግላይፍ 8ቱ መሰረታዊ የጴቀ መዝሙር ትምህርቶችን ለመማር በህብረት ሲሰበሰቡ ለምን? ማን? እንዴት? ከሚለው የትምህርት ዘዴ ቀጥሎ የጉዞ መጀመሪያውን እና 8ቱ የመነሻ  ትምህርቶች መቀጠል አለባችሁ።

ወደ ጌታ ከመራችኋቸው ሰዎች ጋር "**በዙሪያችሁ ያሉትን ሰዎች የሚጻፍበት ወረቀት**"[20 ወይም 100 ዝርዝር] መጠቀም አለባችሁ። ይህ ወረቀት ከመሰል ጴቀ መዛሙርት ጋርም ለእድገታቸው የሚጠቅም መርጃ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡ እናንተም ለራሳችሁ እየተጠቀማችሁ በአመት አንዴ ደግሞ ማሻሻል ይኖርባችኋል። ለምን? ማን? እንዴት? ከሚለው የትምህርት ዘዴ ጋር በማጣመርም መጠቀም አለባችሁ። ወደ ጌታ ካመጣችሁት አንድ ሰው ጋር ትምህርቱን ስትጀምሩ አጠር ባለው የ20 ክርስቲያን ያልሆኑ የስም ዝርዝር መጀመር ትችላላችሁ።

**የኔ ታሪክ(ምስክርተታችሁን የምትነግሩበት)** እና **የእግዚአብሔር ታሪክ(ወንጌል)** የሚባለው ዘዴ አዲስ ወደ ጌታ ካመጣችኋቸው ሰዎች ጋር ወዲያውኑ መጠቀም አለባችሁ። ከመሰል ጴቀ መዛሙርት ጋርም ለእድገታቸው የሚጠቅም መርጃ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም ይቻላል። እናንተም እራሳችሁ እየተጠቀማችሁ በአመት አንዴ ደግሞ ታሪካችሁን ማሻሻል ይኖርባችኋል። ለምን? ማን? እንዴት? ከሚለው የትምህርት ዘዴም ጋር በማጣመር ጥቅም ላይ ይውላሉ።

**የጸሎት ጉዞ** እንደተፈላጊነቱ መጠን መጠቀም አለባችሁ። እናንተም የጸሎት ጉዞን አዘውትራችሁ ማድረግን ልማዳችሁ አድርጉ። ከሌሎች አማኞች ጋር የጸሎት ጉዞ በማድረግ ወደ ሚቀጥለው የእምነት ደረጃ እንዲገቡ እርዷቸው።

**የመጀመሪያ ህብረቶችን** ክርስቲያኖችን ስለ ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ለማሰልጠን መጠቀም ትችላላችሁ ወይም የ3 ወር አጠር ያለ ስልጠና በዛ ላሉ ሰዎች መስጠት ስትፈልጉም ይህን የመጀመሪያ ህብረቶች እንደ ምሳሌ አድርጋችሁ መጠቀም ትችላላችሁ። የመጀመሪያው ሳምንት ላይ ትምህርታችሁን በ ለምን?ማን?እንዴት? ትምህርት ጀምሩ ከዛም በሚቀጥሉት ሳምንታት የመጀመሪያውን ጉዞ በጥልቀት ቀጥሉ።

# ለ3 ወር ቃል መግባት

**ልምምድ: በዙሪያቻችሁ ያሉትን ሰዎች የምትጽፉበት ወረቀት ላይ ያሉትን ስሞች ከታች በሚገኘው ባዶ ቦታ ላይ አስገቡ፡**

**የእኔን ታሪክ** (ምስክርነት) እና **የእግዚአብሔር ታሪክ** (ወንጌል) ለሚከተሉት ሰዎች አካፍላለሁ፡

የሚከተሉትን ሰዎች ከእኔ ጋር ሆነው ህብረት እንዲጀምሩ እጋብዛቸዋለሁ፡

የሚከተሉትን ሰዎች የራሳቸውን ህብረት እንዲመሰርቱ አበረታታቸዋለሁ እንዲሁም ለስራውም አዘጋጃቸዋለሁ፡

የሚከተሉትን ሰዎች በ**ተስፋ፣ የዮሐንስ ምልክቶች** ወይም **የግኝት ህብረት ለፈላጊዎች** ውስጥ እንዲሳተፉ እጋብዛቸዋለሁ፡

የሚከተሉትን ሰዎች የጸሎት ጉዞ ላይ ከእኔ ጋር እንዲሳተፉ እጋብዛቸዋለሁ፡

የሚከተሉትን ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ እና የእግዚአብሔርን ታሪክ እንዲያካፍሉ እና በዙሪያቸው ያሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር እንዲጽፉ በለምን? ማን? እንዴት? የሚባለውን የትምህርት ዘዴ በመጠቀም አሰልጥኜ አዘጋጃቸዋለሁ፡

በሚከተሉት ቤተ ክርስቲያኖች ወይም ቦታዎች ላይ የመጀመሪያው ህብረትን አስጀምራለሁ፡

የጸሎት ጉዞ በየ __________ አደርጋለሁ።

ሌላ ቃል መግባት የምትፈልጉበት ሃላፊነት፡

## የቢግላይፍ መረጃ፡

**ድረ-ገጽ**: www.big.life

**መስጠት**: ሰዎችን በወንጌል እንዲደርሱ እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር እንዲያደርጉ በዓለም የሚገኙትን አማኞችን ማስታጠቅ የሆነውን ራዕያችንን በገንዘብ መደገፍ የምትፈልጉ፣ ድረ-ገጽን ላይ በመግባት መስጠት ትችላላችሁ ወይም ለ" Biglife" ብላችሁ ቼክ ላይ በመጻፍ ከታች ባለው የመልዕክት ሳጥን ቁጥር አድራሻ መላክ እና መርዳት ትችላላችሁ።

**Biglife**
**የመ.ሳ.ቁ. 110431**
**Naples, FL 34108**

**ጸሎት**: የቢግላይፍ ሳምንታዊ የጸሎት ኢሜል እንዲደርስዎት በቢግላይፍ ድረ-ገጽ ላይ ገብተው መመዝገብ ይችላሉ።

**ስልጠና**: ለራስዎ ወይም ለሌሎች ስልጠና ሲፈልጉ training@big.life በሚለው የኢሜል አድራሻችን ሊልኩልን ይችላሉ።

---

## የስልጠና መርጃ፡

**የማሰልጠኛ መጽሐፍት**: ስልጠና በሚለው የድረ-ገጽ ክፍል ውስጥ ማግኘት ያልቻላችሁት የስልጠና መጽሐፍ ወይም ሌላ የስልጠና መርጃዎች ከፈለጋችሁ training@big.life በሚለው የቢግላይፍ አድራሻ በኢሜል መጠየቅ ትችላላችሁ።

**የመማሪያ አካሊት እና ምንጮች**:
https://big.life/training/

# ተጨማሪ መረጃዎች በሚቀጥሉት ገጾች ላይ ይገኛሉ

# ጥምቀት

ጥምቀት ማለት እኛን ከ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እና ከሙታን መነሳት ጋር ስዕላዊ በሆነ የወንጌል ምልክት ተካፈይ የሚያደርገን ነው። ይህም ሁልጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በማመን ይታጀባል እንጂ ጥምቀት ብቻውን አያድንም ፣ ጥምቀት ከእምነት ጋር ሲጣመር ለእግዙአብሔር ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታ ለመከተል ፣ የመናዘዝ ድርጊት ነው [ሮሜ 10፡9-10]፡፡
የሚከተሉትን የሐዋሪያት ሥራ ክፍሎች አንብቡ፡ ምንድን ነው የሆነው?

- 2፡ 37-41
- 9፡ 17-19
- 18፡ 8
- 22፡ 14-16

**አራት ጥያቄዎች፡**

1. ማን ተጠመቀ? [የሐዋ.ሥራ 2፡ 38]
2. መቼ ተጠመቁ? [ካላንደር ወይስ የተሞላ ሰዓት]
3. ማን ነው የሚያጠምቀው? [ማቴ. 28፡19, ዮሐ. 4፡2, የሐዋ. ሥራ 8፡ 35-38፤ 10፡ 47-48]
4. እንዴት ነው የምናጠምቀው? [ማር. 1፡ 9-10]

መጠመቅ ካለባችሁ፡ ማን ነው ሊያጠምቃችሁ የሚገባው? መቼስ ነው መጠመቅ ያለባችሁ? ቀድማችሁ የተጠመቃችሁ ከሆነ፡ የመጽሐፍ ቅዱሱን የጥምቀት ስርዓት ተከትላችኋል? ሰማችሁ፣አመናችሁ፣ተጠመቃችሁ? ይህን አሁን መወያየት ትፈልጋላችሁ?

በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት፡ ጥምቀት የሚደረገው ልክ አንድ ሰው አምኖ ንሰሓ ለመግባት እና ክርስቶስን ለመከተል ሲመርጥ ወዲያው ነው፡ ብዙ ጊዜ ሰውየው ባመነ በሰዓታት ውስጥ ነው፡፡

**የጥምቀት መመሪያዎች**
ወደ 1 ሜትር የሚጠጋ ጥልቀት ያለው ውሃ ላይ መቆም፣ የሚጠመቀው ሰው በሁለት እጆቹ የግራ እግህን ይያዝ፡፡ ቀኝ እጅህን ደግሞ በጀርባው ላይ አድርግ፡፡ የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ጠይቀው እናም አዎንታዊ መልሱን ስማ

> *"ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታህ እና አዳኝህ ተቀብለሃል? እንደ ንጉስህ አድርገህ በቀረው ዘመንህ ልትታዘዘው እና ልታገለግለው ትፈልጋለህ?"*

ከዚያም የሚከተለውን በል:

> *"በተናገርከው ጌታ ላይ ባለህ እምነት መሰረት፡ አሁን በአብ፣ በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ፡፡"*

በግራ እጅህ ወደ ውሃው በምታስገባው ጊዜ ከጉልበቱ ሰበር እንዲል እና ወደ ኋላ ዘመመ እንዲል ንገረው፤ የራስህን እና የተጠማቂውን እጅ ወደ ፊቱ በማምጣት፡ በቀኝ እጅህ ደግሞ ከኋላ በኩል በመርዳት ወደ ኋላቸው ወደ ውሃው ውስጥ ሙሉ ለሙሉ አስጠልቀው፡፡ ከዚያም ከውሃው ውስጥ ወደላይ በማንሳት አውጣው፡፡

# የጌታ እራት [ቁርባን]

1. ቂጣውን እና የወይን ጭማዊውን ወይም ወይኑን አዘጋጁ።
2. ህብረታችሁ በጥሞና ፣ ኃጢያታቸውን በመናዘ የተወሰነ ሰዓት ያሳልፉ።
3. Read 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥ 23-24: “እኔ ከጌታ የተቀበልሁትን አስተላልፌአለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት ሌሊት፣ እንጀራን አንስቶ ከባረከ በኋላ ቆርሶ፣ “ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ለመታሰቢያዬ አድርጉት” አለ።”
4. የህብረቱ አባላት ቂጣውን እንዲበሉ ንገሯቸው።
5. 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥25 ማንበብ ቀጥሉ: “እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ፣”ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ ስለዚህ ከጽዋው በምትጠጡበት ጊዜ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት” አለ።”
6. የህብረቱ አባላት ወይኑን ወይም የወይን ጭማቂውን እንዲጠጡ ንገሯቸው።
7. 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥ 26: " ይህን እንጀራ በምትበሉበት ጊዜ፣ ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ።“
8. በጸሎት እና በዝማሬ የጌታ እራቱን ፕሮግራም ደምድሙ።

# ክርስቲያን ላልሆኑ የህብረት ስብሰባ አቀራረብ

ይህ 3/3ኛን ሂደት ለሚጠቀሙ ክርስቲያን ላልሆኑ ህብተቶች ቀለል ባለ መልኩ የቀረበ ነው። ሦስት ሦስተኛን ቀለል ለማድረግ መለወጥ ቢኖርባችሁም፣ ለመንፈሳዊ እድገታቸው ትክክለኛውን መንገድ ለማስቀመጥ ሂደቱን ለመከተል ሞክሩ። አስታውሱ፣ ሰዎችን የምታስተምሩአቸው እንዲሰሙ፣ እንዲታዘዙ እና የተማሩትን ደግሞ ለሌሎች እንዲያስተላልፉ ነው። ሌሎች መሰረታዊ ነገሮችን ለምሳሌ ፦ ራዕይን ማካፈል እና ልምምድ ወዲያው መጨመር አለባቸው ነገር ግን እነዚህ በህብረት ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ዝግጁ ሲሆኑ ነው።

**ማስታወሻ:** በየሳምንቱ ያለው የህብረቱ መሰባሰብ በእናንተ መሪነት ብቻ ላይ እንዳይንጠለጠል፣ በህብረት ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ሰዎች ከታች ባለው አቀራረብ መሰረት የአብሮነት ጊዜውን እንዲመሩ አድርጓቸው። ከታች የሚገኙትን ጥያቄዎች በአዲስ ወረቀት ላይ ገልብጣችሁ የህብረቱን የውይይት ጊዜ እንዲመራ ለጠየቃችሁት ሰው ስጡት። ይህ ሂደት መሪዎችን ለማሳደግ ይረዳችኋል።

## ወደ ኋላ ተመልከቱ

**መንከባከብ።** ከአብሮነት ጊዜው በኋላ ወይም በፊት ሻይ/ቡና ወይም ምግብ አብራችሁ ተቋደሱ። በዚህ ሳምንት ያጋጠማችሁን ነገር ወይም የተመለሰላችሁን የጸሎት ርዕስ አካፍሉ። ሳምንታቸው እንዴት እንዳለፈ ጠይቁ። እየታገለ ያለ ማንም ሰው ካለ ለእነርሱ ጸልዩ። ከፕሮግራሙም በኋላ ቀይታችሁ አግኟቸው።

**ምርመራ/ማርጋገጥ**።
*እንደሚከተለው ጠይቁ : "ባለፈው ሳምንት የተነበበው መልዕክት እንዴት እንደተናገረህ እና ምን ማድረግ እንደምትፈልግ ተናግረሃል። አደርጋለሁ ያልከውን ነገር ማድረግ ቻልክ?"*

## ወደላይ ተመልከቱ

**ጸሎት።** አጠር አድርጋችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ። የዚህን ሳምንት ምንባብ ደግሞ እንዲያስተምራችሁ ጠይቁት።

**ማንበብ እና መወያየት።** የዚህን ሳምንት ምንባብ አንብቡ።

- *ከዚህ ምንባብ ውስጥ **የወደዳችሁት** ነገር ምንድን ነው?*
- *በዚህ ምንባብ ውስጥ በህይወታችሁ ለመፈፀም **የከበዳችሁ** ነገር ምንድን ነው?*

የዚህን ሳምንት ምንባብ እንደገና አንብቡ።

- *ይህ ምንባብ ስለ **እግዚአብሔር** ምን ያስተምራል?*
- *ይህ ምንባን ስለ ሰዎች ምን ያስተምራል?*

## ወደ ፊት ተመልከቱ

**ታዘዙ እና ተናገሩ።** አሁን በህብረታችሁ ውስጥ ሆናችሁ ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዴት እንደምትመልሱ አስቡ። በህብረታችሁ መጸለይ ከተቻለ፣ እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት መመለስ እንደምችሉ ጸልዩ። ለአንዱም ሆነ ለሁለቱም ጥያቄዎች መልስ ካገኛችሁ ለህብረቱ አካፍሉ።

*ይህ ምንባብ ለግላችሁ ምን ተናገራችሁ? ልታደርጉት የሚገባ/ማድረግ ያለባችሁ ነገር አለ? ይህን የሰማችሁትን ነገር የምትነግሯቸው እግዚአብሔርን በበለጠ መልኩ እንዲያውቁት የምትፈልጉት ሰዎች አሉ?*

# ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች ህብረት የጥናት ጉዞ

የሚከተሉትን የምንባብ ክፍሎች የተስፋ ወይም የዮሐንስ ምልክቶች ተከታታይ ትምህርቶች ላይ ያለውን “ወደላይ ተመልከት” ክፍል ላይ ተጠቀሙት። ለአንዳንዱ ምንባቦች ከአንድ በላይ ስብሰባ ለህብረታችሁ ሊያስፈልግ ይችላል።

## የተስፋ ተከታታይ ትምህርት [ለሚፈልጉት]

1. ተስፋ ለኃጢያተኞች: የሉቃስ ወንጌል 18፥9-14
2. ተስፋ ለድሆች: የሉቃስ ወንጌል 1213-34
3. ተስፋ ለኮብላዩ: የሉቃስ ወንጌል 15፥11-32
4. ተስፋ ለጠፉት: የሉቃስ ወንጌል 19፥1-10
5. ተስፋ ለአዘኑት: የዮሐንስ ወንጌል 11፥1-44
6. ተስፋ ለሚፈልጉት: የዮሐንስ ወንጌል 3፥1-21

## የዮሐንስ ምልክቶች [ለሚፈልጉት]

1. ውሃውን ወደ ወይን የለወጠ: የዮሐንስ ወንጌል 2፥ 1-12
2. የንጉሥ ቤት ሹም ልጅ መፈወስ: የዮሐንስ ወንጌል 4፥ 46-54
3. የሽባው መፈወስ: የዮሐንስ ወንጌል 5፥ 1-17
4. 5000ውን መመገብ: የዮሐንስ ወንጌል 6፥ 1-14
5. በውሃ ላይ መራመዱ: የዮሐንስ ወንጌል 6፥ 15-25
6. ዕውር ሆኖ የተወለደውን መፈወሱ፡ የዮሐንስ ወንጌል 9፥1-41
7. አልዓዛርን ከሙታን ማስነሳቱ: የዮሐንስ ወንጌል 11፥1-46
8. ወደ አብ የሚያስገባን ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ ነው: የዮሐንስ ወንጌል 14፥1-11

# የመረዳት ተከታታይ ትምህርቶች

[የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ ዳራን ለሚፈልጉ ህብረቶች ወይም በደንብ ለማወቅ ለሚፈልጉ ወይም ለፈላጊ ህብረቶች]

የሚከተሉትን ምንባቦች በህብረታችሁ ውስጥ ያለውን "ወደላይ ተመልከት" የሚለው ክፍል ላይ ተጠቀሙት። ለአንዳንዱ ምንባቦች ከአንድ በላይ ስብሰባ ለህብረታችሁ ሊያስፈልግ ይችላል።

## እግዚአብሔርን እወቁት - እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እና ምን እንደሚመስል

1. ፍጥረት - ዘፍጥረት 1
2. የሰው መፈጠር - ዘፍጥረት 2
3. የሰው አለመታዘዝ - ዘፍጥረት 3
4. ኖኅ እና ጎርፉ - ዘፍጥረት 6:5-8:14
5. እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባው ቃልኪዳን- ዘፍጥረት 8:15-9:17
6. እግዚአብሔር ለአብረሃም ተናገረው - ዘፍጥረት 12፥1-7፤ 15፥1-6
7. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው[ኃጢያት የለበትም] - ዘሌዋውያን 19:2፤ ዘዳግም 32:3-4
8. እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ትዕዛዛት- ዘጸአት 20፥1-21
9. የአብረሃም ዘር ላይ ዳዊት መንገሱ - 1ኛ ሳሙኤል 16፥1-13፤ 2ኛ ሳሙኤል 7፥1-28
10. ንጉስ ዳዊት እና ቤርሳቤህ - 2ኛ ሳሙኤል 11፥ 1-27
11. የናታን ታሪክ - 2ኛ ሳሙኤል 12፥1-25
12. ዳዊት ለሰራው ኃጢአት ምህረትን ጠየቀ - መዝሙረ ዳዊት 51፥1-17
13. አዳኝ እንደሚመጣ እግዚአብሔር ቃል ገባ - ኢሳይያስ 53

## ኢየሱስን እወቁ - ኢየሱስ ማን እንደሆነ እና ለምን እንደመጣ

1. አዳኙ ተወልዷል - የማቴዎስ ወንጌል 1፥ 18-25
2. የኢየሱስ ጥምቀት - የማቴዎስ ወንጌል 3፥ 7-9, 13-15
3. እብዱ ሰው ተፈወሰ -የማርቆስ ወንጌል 5፥ 1-20
4. ኢየሱስ መቼም ቢሆን በጎቹ አይጠፉበትም - የዮሐንስ ወንጌል 10፥ 1-30
5. ኢየሱስ ዕውሩን ፈወሰ -የሉቃስ ወንጌል 18፥ 31-42
6. ኢየሱስ እና ዘኬዎስ - የሉቃስ ወንጌል 19፥ 1-9
7. ኢየሱስ እና ማቴዎስ - የዮሐንስ ወንጌል 9፥ 9-13
8. ኢየሱስ ኃጢያት የለሽ ነው -ዕብራዊያን 4፥ 14-16፤ 10፥ 1-14
9. ኢየሱስ ብቻኛው መንገድ ነው -የዮሐንስ ወንጌል14፥ 1-15
10. መንፈስ ቅዱስ ይመጣል - የዮሐንስ ወንጌል 16፥ 5-15
11. የመጨረሻው እራት - የሉቃስ ወንጌል 22፥ 14-20
12. የኢየሱስ መያዝ እና ወደ ፍርድ መቅረብ -የሉቃስ ወንጌል 22፥47-53፤ 23፥13-24
13. የኢየሱስ መሰቀል - የሉቃስ ወንጌል 23፥ 33-56
14. ኢየሱስ በህይወት አለ -የሉቃስ ወንጌል 24፥ 1-7, 36-47፤ Acts 11-11
15. ኢየሱስ አንድ ቀን በዓለም ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ ይመጣል - 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥16-17፤ የዮሐንስ ወንጌል 25፥31-46

## ክርስትና ህይወትን ተረዱ - እንደ ክርስቲያን እንዴት መኖር አለብን?

1. ክርስቲያን የሆነው በኢየሱስ አምነን፣ የሰራነውን ኃጢያት ይቅር እንዲለን የጠየቅነው ጊዜ ነው - የሐ.ሥራ 2፥ 36-41
2. የደህንነት ዋስትና/ማረጋገጫ – 1ኛ ዮሐንስ 5፥ 11-13፤ ኤፌሶን 1፥ 13-14
3. የይቅር መባላችን ዋስትና/ማረጋገጫ - 1ኛ ዮሐንስ1፥ 9
4. መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖሩ - የዮሐንስ ወንጌል 14፥15-18፤ ቲቶ 3፥ 4-6
5. መንፈስ ቅዱስ በህይወታችን ፍሬ ማፍራቱ - ገላትያ 5፥ 22-23
6. ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ህብረት ማድረግ - ዕብራውያን 10፥ 24-25
7. ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ [ጸሎት እና ቃሉን ማንበብ] - የማርቆስ ወንጌል 1፥ 35; መዝሙረ ዳዊት 19፥ 7-11
8. ኃጢያትን ድል በመንሳት - 1ኛ ጴጥሮስ 1፥ 13-25 ፤ 2፥ 1-3

9. በፍቅር በመኖር -የማቴዎስ ወንጌል 22፥ 36-40; 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥ 1-7
10. ደቀ መዛሙርትን ማፍራት እና የኢየሱስን ትዕዛዛት እንዲያከብሩ ማስተማር - የማቴዎስ ወንጌል 28፥ 19-20
11. በልግስና መስጠት – 1ኛ ቆሮንቶስ 16፥ 1-2፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 9፥ 6-8
12. እግዚአብሔር የሰጠንን የፀጋ ስጦታዎችን መጠቀም - ሮሜ 12፥ 1-8

# የማጠናከሪያ ተከታታይ ትምህርት

[ደቀ መዝሙርነት ላይ ማተኮር ለሚፈልጉ አዲስ አማኞች ወይንም ህብረቶች]

7ቱን የኢየሱስ ዋና ትዕዛዛትን ለመጠበቅ/ለማክበር መማር። በዝርዝራችሁ ላይ ላሉት ሰዎች ስለ ኢየሱስ ማካፈል ቀጥሉ።

1. መማር እና መተግበር -የዮሐንስ ወንጌል 14፥ 15-21
2. ነስሓ ግቡ። እመኑ። ተከተሉ። የማርቆስ ወንጌል 1:14-17, ኤፌሶን 2:1-10
3. ተጠመቁ - የማቴዎስ ወንጌል 28፥ 19፤ የሐ.ሥራ 8፥ 26-38
4. እግዚአብሔርን ውደዱ። ሰውንም ውደዱ - የሉቃስ ወንጌል 10፥ 25-37
5. ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ - የማቴዎስ ወንጌል 6፥ 9-13. የኢየሱስን ጸሎት ተማቱት እናም ተለማመዱ
6. ኢየሱስን አስታውሱት አክብሩትም- የሉቃስ ወንጌል 22፥ 14-20፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥ 23-32
7. ስጡ -የሐ.ሥራ 4፥ 32-37
8. አስተላልፉ - የማቴዎስ ወንጌል 28፥ 18-20

እኔ እንደተከተልኩት ተከተሉ። ደቀ መዛሙርቶችን አፍሩ። የተማራችሁትን ለሌሎች አስተላልፉ። እነርሱም ለሌሎች እንዲያስተላልፉ አስተምሯቸው

1. ደቀ መዝሙር ፈልጉ [ጢሞቴዎስ የጳውሎስ ደቀ መዝሙር ነበር] – 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥ 1-14
2. የተማራችሁትን ለሌሎች አስተላልፉ፤ እነርሱም ለሌሎች ተመሳሳይ እንዲያደርጉ አስተምሩ - 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥ 1-4፣ 14-16
3. በተማራችሁበት ነገር ቀጥሉ፤ የሳሰት አስተማሪዎችን ተጠንቀቁዋቸው - 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥ 1-17
4. ጽኑ እንዲሁም ተዘጋጁ - 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥ 1-8

ህብረታችሁን አባዙ። ደቀ መዛሙርቶቻችሁን ሰብስባችሁ በአንድ ህብርት አድርጉ።

1. ዕቅድ በመስራት ጀምሩ፤ የሰላም ሰዎችን ፈልጉ። የሉቃስ ወንጌል 10፥ 1-11. አዲስ ህብረት በምትጀምሩበት ጊዜ የኢየሱስን ትዕዛዛት አዳምጡ።
2. አንድ ላይ ተሰብሰቡ - የሐ.ሥራ 2፥ 36-47
3. የሰላም ሰው [ክፍል 2] - የማርቆስ ወንጌል 5፥ 1-20። ስለ ኢየሱስ ታሪክ ለመናገር ፍቃደኛ የሆኑትን ፈልጉ። ከዚህ ሰው ጋር፣ ከቤተሰቦቹ እና ከጓደኞቹ ጋር ሆናችሁ ህብረትን ጀምሩ።
4. ማን ነው ዝግጁ - የማቴዎስ ወንጌል 13፥ 1-9፣ 18-23

ወደ አካባቢያችሁ ሂዱ። አካባቢያችሁ ያሉትን ሰዎች እንዴት በወንጌል እንደምትደርሱ ተማሩ።

1. ሂዱ: ወደ አካባቢያችሁ- የሐ.ሥራ 1፥ 1-8
2. ድኾችን እርዱ ። የምስራቹን ተናገሩ - የሉቃስ ወንጌል 7፥ 11-23
3. እግዚአብሔር ወደ ሚልካችሁ ሁሉ ሂዱ - የሐ.ሥራ 10፥ 9-48
4. ከዕቅድ ጋር ሂዱ - የሐ.ሥራ 13፥ 1-3፣ 32-33፣ 38-39፣ 14፥ 21-23፣ 26-27

ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ። እንዴት የምድር ዳርቻ ድረስ ሰዎችን እንደምትደርሱ ተማሩ።

1. ሂዱ: ወደ ዓለም ሁሉ - የሐ.ሥራ 1፥ 1-8, የማቴዎስ ወንጌል 28፥ 19-20
2. እግዚአብሔር ወደ ሚልካችሁ ሁሉ ሂዱ - የሐ.ሥራ 8፥ 26-40
3. እግዚአብሔር ሁሉንም ሕዝብ ይወዳል - የዮሐንስ ወንጌል 4፥ 4-30፣ 39-41፤ የዮሐንስ ራእይ 7፥ 9-12
4. ከዕቅድ ጋር ሂዱ - የሐ.ሥራ 13፥ 1-3፣ 32-33፣ 38-39፤ 14፥ 21-23፣ 26-27

መሰረታዊ ነገሮችን አስታውሱ። ስትሰበሰቡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ አስታውሱ።

1. ኢየሱስ የመጀመሪያው ነው - ፊልጵስዩስ 2፥ 1-11
2. ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ - የማቴዎስ ወንጌል 6፥ 5-15
3. ህዝብ - ዕብራውያን 10፥ 23-25
4. መጽሐፍ ቅዱስ – 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥ 10-17

መስጠት ። ኢየሱስን እስከ መጨረሻው በርትቶ መከተልን ተማሩ።

1. አለመታዘዝ - ትንቢተ ዮናስ 1
2. መስጠት - ትንቢተ ዮናስ 2
3. መታዘዝ - ትንቢተ ዮናስ 3
4. እስከ መጨረሻው መታዘዝ -ትንቢተ ዮናስ 4

ከዚያ የት? የራሳችሁን የምንባብ ክፍል ምረጡ እና መሰባሰባችሁን ቀጥሉ። ተመሳሳይ ጥያቄዎችን እና የህብረት ስብሰባ አሰራርን ተጠቀሙ።

**ለምን እግዚአብሔር እኛን አዳረን?** ስለሚወድደን [የዮሐንስ ወንጌል 3፡16-18]። ይህን የፍቅሩን እና የምህረቱን መልካም ዜና ለሌሎች እንድናበስር እግዚአብሔር ይፈልጋል።

## 4ቱ ትዕዛዛት [የማቴዎስ ወንጌል 28፡ 19-20]

1. ሂዱ
2. ደቀ መዛሙርት አድርጉ
3. አጥምቁ
4. ትዕዛዛትን እንዲጠብቁ አስተምሯቸው

## 4ቱ ጥሪዎች

1. ከላይ የመጣ ጥሪ: የማርቆስ ወንጌል 16፡15
2. ከታች የመጣ ጥሪ: የሉቃስ ወንጌል 16፡ 27-28
3. ከውስጥ የወጣ ጥሪ: 1 ቆሮንቶስ 9፡16-17
4. ከውጭ የሆነ ጥሪ: የሐዋርያት ሥራ 16፡ 9

## ማን? በዙሪያቻሁ ላሉት፤ 20

**ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሌላቸውን 20 ሰዎችን ባዶ ወረቀት ላይ ዘርዝሩ።** ይህን የስም ዝርዝር ይዛችሁ በፀሎት ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ፤ በሚቀጥለው ሳምንት የእራሳችሁን ታሪክ እና የእግዚአብሔርን ታሪክ የምትነግሯቸውን 5 ሰዎች እንዲያመላክታችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት

## እንዴት? ታሪክዎን ያጋሩ

ከኢየሱስ በፊት ሕይወትህ

እንዴት ኢየሱስን እንዳገኘኸው

እንዴት ነው ኢየሱስ ህይወታችሁን የለወጠው?

?

መልስ ለማግኘት ይጠይቁ ወይም የእግዚአብሔርን ታሪክ ያካፍሉ

## እንዴት? Share God's Story




## የህብረት መሰብሰቢያ ቅፅ [3/3]

### ወደ ኋላ ተመልከት

**መተሳሰብ እና አምልኮ**

**መጠየቅ [የማይዘለል]**

- የተማራችሁትን እንዴት ተገበራችሁት?
- የት ያሰለጥኑ?
- ታሪክዎን ወይም የእግዚአብሔር ታሪኩን ያጋሩት?

**ራዕይ** - ደቀ-መዛሙርቶችን እና ቡድኖችን ማባዛት

### ወደላይ ተመልከቱ

**ጸልዩ**

**ብቡ እና ተወያዩ**

*ከዚህ ክፍል ውስጥ የወደዳችሁት ምንድን ነው?*

*ከዚህ ክፍል እራሳችሁን እንድትወቅሱ/እንድታስቡ ያደረጋችሁ ምንድን ነው?*

**ብቡ እና ተወያዩ**

*ይህ ምንባብ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምራል?*

*ይህ ምንባብ ስለ ሰዎች ምን ያስተምራል?*

### ወደፊት ተመልከቱ

ጸልይ እና እግዚአብሔርን አዳምጥ. የተናገረውንአድምጡ.

**ልምምድ**